# አዲስ ዘመን

እኖድ

እሁድ | 84 ዓመት ቁጥር 019 መስከረም 19 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# “የለሚ የሲሚንቶ ፋብሪካ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን በፍጥነት እና በብቃት አጠናቅቆ ዝግጁ የማድረግ ተምሳሌትም ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የለሚ ብሔራዊ የሲሚንቶ ፋብሪካ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በፍጥነት እና በብቃት አጠናቅቆ ዝግጁ የማድረግ ተምሳሌትም ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤በቀን 150 ሺህ ኩንታል የማምረት አቅም ያለውን የለሚ ብሔራዊ የሲሚንቶ ፋብሪካ መርቀን ሥራ አስጀምረናል። ይህ ሜጋ ፕሮጀክት የመንግሥታችን በፍጥነት፣ በግዝፈት እና በንፅህና የመገንባት ጽኑ አቋማችን ማሳያ ነው። እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በፍጥነት እና በብቃት አጠናቅቆ ዝግጁ የማድረግ ተምሳሌትም ነው።

በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገራችን ያሉ ተመሳሳይ ፋብሪካዎች ተደምረው የሚያመርቱትን ሃምሳ ከመቶ የሚያመርት የሲሚንቶ ፋብሪካ እውን እንዲሆን የተሳተፋችሁ በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ፤እንደ ለሚ ያሉትን የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች በሀገራችን ካባዛን በሥራ ፈጠራ ላይ የሚኖረው የመባዛት ፍሬ አቻ የማይገኝለት ነው ብለዋል።

ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደዚህ ስፍራ ስመለስ የአመራር መርሆዎቻችን ማሳያ በሆነው በሥራው ፍጥነት ተደንቄያለሁ። ፕሮጀክቱ በመሰል ጠንካራ ሥራ መጪው

“የለሚ የሲሚንቶ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በምግብ ራስን መቻል ሌላው ሉዓላዊነት



የስንዴ ልማት አንዱ የምግብ ሉዓላዊነትን የማረጋገጥ ስኬታማ ሥራ ማሳያ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ለመቻልና የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋጋት እየሠራች እንደሆነ ይገለጻል። ለመሆኑ የምግብ ሉዓላዊነት ስንል ምን ማለታችን ነው? የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እየተሠራ ያለው ሥራስ ምን ውጤት እያስገኘ ነው? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉ ምሁራን አስተያየታቸው ሰጥተውናል።

በግብርና ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ሥርዓተ ምግብ ሽግግርና ኒውትሬሽን ዋና አስተባባሪና የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ

በምግብ ራስን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የባህር በር እጦት የወለዳቸው የኢኮኖሚ ሰንኮፎች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ለኢኮኖሚ ስብራቱ ዋነኛ መንስኤ የባህር በር አለመኖሩ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ወደብ የሌላቸው ሀገራትም ብዙ ጊዜ የኢኮኖሚ እድገታቸው ውስን የሚሆነው አንዱ ምክንያት የባህር በር አለመኖራቸው እንደሆነ ይገለጻል። የዓለም ኃያላን ሀገራት በቀይ ባህርና በዙሪያዋ ቦታ ለማግኘት የሞት ሽረት ትግል ሲያደርጉም ይስተዋላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሰጡት ማብራሪያ፤ የባህር በር የአንድ ሀገር ጥቅል የምርት እድገትን ከ25 እስከ 30 በመቶ ከፍ እንደሚያደርገው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥናትን ጠቅሰው መናገራቸው ይታወሳል።

ከዚህ አኳያ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነውን የወጪና ገቢ ንግዷን በጂቡቲ በኩል የምታከናውነው ኢትዮጵያም የባህር በር በማጣቷ ምክንያት በዓመት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለወደብ ኪራይ ታወጣለች። ይሁን

የባህር በር እጦት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ሦስት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ ናቸው

- ከማዕድን የወጪ ንግድ 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል

ገጽ 4
















ዜና

# “ኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ ያለውን የማሪታይም ደህንነት በቅርብ እየተከታተለች ነው”

- አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ ያለውን የማሪታይም ደህንነት በቅርብ እየተከታተለች መሆኗን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ አስታወቁ። የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ወደ ታሪካዊው የትግበራ ምዕራፍ ሊሸጋገር መቃረቡን ጠቁመዋል።



የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ 79ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ በኒውዮርክ ከተማ ሲካሄድ ባደረጉት ንግግር፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ ያለው የማሪታይም ደህንነት ስጋት እጅጉን እንደሚያሳስባት ገልጸዋል።

ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት እና የማሪታይም ንግድን የምትጠቀመው ኢትዮጵያ በውቅያኖሶቹ ያለውን የማሪታይም ደህንነት በቅርብ እየተከታተለች መሆኑን ገልጸው፤ግጭቶች፣ የባህር ላይ ውንብድናና ሌሎች ሕገ ወጥ ተግባራት በአካባቢው ያለውን የማሪታይም ደህንነት አደጋ ላይ መጣሉን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ የማሪታይም ደህንነት ጥበቃ ሥራዎች ሁሉን አሳታፊ እንዲሆኑ ትፈልጋለች ያሉት አምባሳደር ታዬ ፤የባህር በር የማሰስና የመጠቀም ፍላጎቷ ሊከበር እንደሚገባም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችው ስምምነት ከቀጣናው ሀገራት ጋር በጋራ መልማትና መበልፀግን መሠረት ባደረገ መልኩ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በትብብር የመሥራት ልምድ እንዳላት ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ሽብርተኛነትን በመዋጋት ሰላምና ደህንነት እንዲረጋገጥ እየሠራች እንደምትገኝ ገልጸው፤ በሶማሊያ የሽብርተኛ ቡድን የሆነውን አልሸባብን አቅም በከፍተኛ ሁኔታ በማዳከም ረገድ ከሌሎች ሀገራት ሰላም አስከባሪ ኃይሎች ጋር ውጤታማ ተግባር ማከናወኗን አንስተዋል።

በሶማሊያ ሽብርተኝነትን በመዋጋት የተገኙ ድሎችን ስጋት ላይ የሚጥሉ ጉዳዮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስተዋሉ መምጣታቸውንም አመልክተው፤ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በሶማሊያ የተገኙ ድሎችን ወደ ኋላ በመመለስ የቀጣናውን ሰላምና ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ድርጊቶችን ሊያስቆም እንደሚገባ አሳስበዋል።

አምባሳደር ታዬ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሰላም የከፈለችውን መስዋዕትነትና ዋጋ እውቅና ልትሰጥና ልታከብር እንደሚገባም ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ከቀጣናው ሰላምና መረጋጋት በተገናኘ የሚቀርቡባትን ክሶችና ወቀሳዎች በፍጹም አትቀበልም፡፡ ሽብርተኝነትን ከመዋጋት የሚያግዳት ምንም ነገር እንደሌለም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ እንዲሁም ለውጤታማ የባለብዙ ወገን የትብብር መድረክ በቁርጠኝነት ትሠራለች ነው ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቋሚ ውክልና ማግኘት እንደሚገባት ገልጸዋል።

ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ሥርዓት ላይ ጥልቅ ማሻሻያ በማድረግ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት ፍትሐዊ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኙ የሚመለከታቸው ሁሉ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል።

በሌላ በኩል የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ወደ ታሪካዊው የትግበራ ምዕራፍ ሊሸጋገር መቃረቡን ገልጸው፤ ይህም በተፋሰሱ ሀገራት ፍትሐዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቀም እንዲኖር ያደርጋል ነው ያሉት።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መጀመሩንና ይህም የኢትዮጵያንና የጎረቤት ሀገራትን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት በመመለስ ቀጣናዊ ትብብርን ለማጎልበት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ40 ቢሊዮን ችግኝ መተከሉን ጠቁመው፤አረንጓዴ አሻራ የኢትዮጵያን የደን ሽፋን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደጉንም ገልጸዋል።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል።

# የግብጽ ያልተገባ እንቅስቃሴ መላ አፍሪካውያንን የሚያስቆጣ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ግብጽ ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር በጎረቤት ሀገራት እያደረገችው ያለው የስህተት እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ አልፎ መላ አፍሪካውያንን የሚያስቆጣ መሆኑ ተገለጸ፡፡

ታዋቂው ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተንታኝ አቶ ሙሳ ሸኮ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ግብጽ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ የሚለውን መርህ በመጣስና ኢትዮጵያ ላይ አሉታዊ ጫና ለመፍጠር እንደ ሶማሊያ፣ ኤርትራ እና ደቡብ ሱዳን ባሉ ሀገራት የምታደርገው ያልተገባ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ አልፎ መላ አፍሪካውያንን የሚያስቆጣ ነው፡፡

ግብፅ በኢትዮጵያ ላይ የውጭ ጫና ለመፍጠር የምትሞክረው በተለይም እንደ ሶማሊያ፣ ኤርትራ እና ደቡብ ሱዳን ባሉ ሀገራት የምታደርገው አሉታዊ እንቅስቃሴ የአፍሪካ መፍትሔዎችን መርህ የሚጻረር ነው ያሉት አቶ ሙሳ፤ እነዚህ ድርጊቶች ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ብሎም መላውን የአፍሪካ አህጉር ሕዝብ የሚያስቆጣ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

አቶ ሙሳ፤ ግብፅ የኢትዮጵያን እድገት ለማዳከም የረዥም ጊዜ ታሪክ እንዳላት ጠቁመው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከዓባይ ግድብ ግንባታ ጋር በተያያዘ የተሳሳተ አቋም እየወሰደች መሆኗን ገልጸዋል፡፡ ግብፅ የግድቡ ግንባታ ለአካባቢው የሚያስገኘው ጥቅም ወደ ጎን በመተውና ዓባይ የእኔ ብቻ በሚል የተሳሳተ እሳቤ የተለያዩ ጫናዎችን ማድረጓንም አንስተዋል፡፡

ይህንኑ ጫናዋን በማጠናከር በቅርቡ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት ለማግለል ከሶማሊያ ጋር ወታደራዊ ጥምረት በመፍጠር፣ ከኤርትራ ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና “የሰላም መልዕክተኞች” በሚል ወደ ደቡብ ሱዳን ወታደሮችን ለመላክ በማቀድ በኢትዮጵያ ዙሪያ እየተሽከረከረች ትገኛለች ነው ያሉት፡፡

እነዚህ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደርና በቀጣናው ውስጥ ያለውን አንድነት ለማዳከም የምትሠራው ስትራቴጂ አካል እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

በሶማሊያ የምታደርገው እንቅስቃሴ ምንም እንኳን ጥቂት ደጋፊዎቿን ቢያስደስትም የፖለቲካ ልሂቃንን ጨምሮ አብዛኛው የሶማሊያ ሕዝብና ሌሎች አፍሪካውያን ድርጊቷን እየተቃወሙ እንዳለም አስታውቀዋል።

አካሄዷ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ መላ አፍሪካውያንን የሚያስቆጣ ነው በማለት፤ በርካቶችም እንቅስቃሴዋን ለቀጣናውም ሆነ ለሰፊው አፍሪካዊ አንድነት መሸርሸር መንስዔ ሊሆን እንደሚችል እየተቹ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡


ወቅታዊው የግብፅ ድርጊት የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ሰላምና እድገትን ለማደፍረስ የተደረጉ ታሪካዊ ሙከራዎቿ ቀጣይነት አመላካች ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም ይህ የግብጽ ታሪካዊ የሆነ የዲፕሎማሲ ስህተትና ጠላትነትን ይፋ የማድረግ አካሄድ ራሷን ግብጽን አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ግብፅ ኢትዮጵያንና የምሥራቅ አፍሪካን ቀጣና ለማተራመስ የምታደርገው ጥረት የረዥም ጊዜ የጣልቃ ገብነት አካል ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ፅናት እንደሚያሳየው ግን አሁንም እነዚህ ፈተናዎችን መወጣት እንደምትችል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል ከ389 በላይ የቱሪስት መዳረሻ ዋሻዎች በጥናት ተለይተዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከ389 በላይ የቱሪስት መዳረሻ ዋሻዎች በጥናት እንደተለዩ የክልሉ ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።



የቢሮው የቱሪዝም ልማትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር አቶ ፋንታሁን ታደሰ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ይገኛሉ፡፡ ከክልሉ የቱሪስት መዳረሻዎች መካከል የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ዋሻዎች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። በአሁኑ ጊዜም በክልሉ ከ389 በላይ የቱሪስት መዳረሻ ዋሻዎች በጥናት ተለይተዋል፡፡

የክልሉን እምቅ የቱሪዝም ሀብት በአግባቡ በማስተዋወቅ እና በማልማት ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ፋንታሁን፤ ለዚህም በክልሉ ከ389 በላይ የቱሪስት መዳረሻ ዋሻዎች በጥናት እንደተለዩ ገልጸዋል።

ለእነዚህ ካርታና ፕላን እንዲሁም ዋሻዎቹ እንዲጎበኙ የመሠረተ ልማት ሥራዎች እየተሟሉ መሆኑን የተናገሩት አቶ ፋንታሁን፤ የክልሉ መንግሥት የሕዝቡን የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ለመመለስ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። በተለይም በቱሪስት መዳረሻዎች አካባቢ የሚስተዋለውን የመንገድ መሠረተ ልማት ችግር በመፍታት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷል ብለዋል።

ከተለዩት ከ389 በላይ የቱሪስት መዳረሻ ዋሻዎች ውስጥ የናሲአል ዋሻ አንዱ ነው። በአካባቢው እንደ መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት፣ የቱሪስት ማረፊያና የእንግዳ መቀበያ መሠረተ-ልማቶች ለማሟላት እየተሠራ ነው። ዋሻውን በማልማትና በማስፋፋት የሀገራችን ብሎም የአህጉራችን ምርጥ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ ቢሮው ከምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጋር በመተባበር ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ይህም በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ ገልጸው፤ ዋሻውን ለመጎብኘት የሚመጡ የውጭና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች እግረ-መንገዳቸውን ሌሎች የተፈጥሮ ዋሻዎችን፣ ደኖችን ጨምሮ አዕዋፋትና የዱር እንስሳትን እና መሰል የቱሪስት መስህቦችን ለመጎብኘት ልዩ እድል ይፈጥራል ነው ያሉት።

ክልሉን በቱሪዝም ዘርፍ ተወዳዳሪ ማድረግ ለሥራ ፈጠራ፣ ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ለሳይንሳዊና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የገለጹት አቶ ፋንታሁን፤ በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም ፀጋዎችን አልምቶ ውጤታማ የማድረግ ኃላፊነት የማህበረሰቡን ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑን ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያውያን ብልፅግናቸውን ተጨባጭ ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው!

ኢትዮጵያውያን ለፍትሕ እና ለሉዓላዊነታቸው በየዘመኑ ብዙ ዋጋ በመክፈል ከሚታወቁ ጥቂት የዓለም ሀገራት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህም ለዘመናት ሉዓላዊነታቸውን ማስከበር ችለዋል፤ ለብዙዎችም የፍትሕ እና የነፃነት ትግል ፋናወጊ፤ የአልገዛም ባይነት ተምሳሌት ሆነዋል።

ረጅም ዘመናት በሚቆጠረው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ታሪካቸው፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ የተገደዱ፤ ከእያንዳንዱ ፈተና ጽናት እና ጥንካሬን በመማር፤ በየዘመኑ በሉዓላዊነታቸው ላይ የተነሱ የውጪ ኃይሎችን ከፍ ባለ ተጋድሎ አንገት አስደፍቶ በመመለስ የደመቀ ታሪክ ባለቤት የሆኑ ሕዝቦች ናቸው።

በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ በሉዓላዊነታቸው ላይ የማይደራደሩ፤ ከጠላቶቻቸው ማንነት ይልቅ፤ በትናንት የነፃነት ታጋድሎ ታሪካቸው እና ታሪኩ ባጎናጸፋቸው ብሔራዊ ክብር እና ማንነት ሁሌም ጠላቶቻችውን አሸንፈው የአሸናፊነት ትርክታቸውን ለማስቀጠል ከራሳቸው ጋር መክረው በጽናት የሚቆሙ ሕዝቦች ናቸው።

ለሀገር ነፃነት እና ለሕዝቦች ብሔራዊ ክብር መሞት ለኢትዮጵያውያን ዘመናት የተሻገረ፤ በአንዳንዱ ትውልድ ውስጥ የእስትንፋስ ያህል ትርጉም ያለው፤ ከቀደመው ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ትውልዶች ለሀገር መሞት ክብር እንደሆነ አውቀው እና ተረድተው ራሳቸውን ለመስዋዕትነት ሁሌም ዝግጁ እንዲያደርጉ ያስቻለ ነው።

ይህን ደግሞ ከሁሉም በላይ ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚመሰክሩት፤ በየዘመኑ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመዳፈር ባደረጓቸው ያልተሳኩ ሙከራዎች ብዙ ዋጋ ከፍለው በተጨባጭ ያረጋገጡት እውነታ ነው። በታሪካቸው ያልተገባ ድፍረት እና እብሪት ያልተጠበቀ ዋጋ እንደሚያስከፍል የተማሩበትን ዕድል የፈጠረላቸውም መልካም አጋጣሚ ጭምር ነው።

ዛሬ ላይ ይህንን እውነታ በመዘንጋት እነዚህ ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚያደርጓቸው የጠባጫሪነት እንቅስቃሴዎች፤ አንድም ከትናንት ተመሳሳይ የታሪክ ስህተት ያለመማር፤ ከዚያም ባለፈ የኢትዮጵያውያንን ዘመን ተሻጋሪ የሉዓላዊነት የተጋድሎ ታሪክ ከመዘንጋት የሚመነጭ አላሳቢነት ነው።

ኢትዮጵያውያን እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ለፍትሕ እና ለፃነት ቀናኢ ናቸው፤ የማንንም ሀገር ሕዝብ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትንም ሆነ ሉዓላዊነት ያከብራሉ፤ በተለይም በአካባቢው የሚገኙ ሀገራት ሕዝቦች ካላቸው ቤተሰብነት አንጻር፤ ከማንም በላይ ከነዚህ ሕዝቦች ጋር ለጋራ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት አብዝተው ይሠራሉ።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ብሩህ ሊሆን የሚችለው ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች አቅሞች አቀናጅቶ መጠቀም የሚያስችል ልማትን ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል እንደሆነ አብዝተው ያምናሉ ፤ እያንዳንዱ የልማት እንቅስቃሴያቸውም ይህንኑ እውነታ ታሳቢ ያደረገ ነው።

ኢትዮጵያውያን በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ፤ የማንንም ሀገር ሉዓላዊነት ሆነ ብሔራዊ ጥቅም አደጋ ውስጥ የሚከት እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል የአስተሳሰብ መዛነፍ የላቸውም፤ በረጅሙ የሀገረ መንግሥት ታሪካቸውም በዚህ መልኩ የተጻፈ ታሪክ የላቸውም። ወደፊትም ሊኖራቸው ይችላል ብሎ ማሰብም የሕዝቡን ማኅበረሰባዊ ማንነት ካለመረዳት የሚመነጭ ይሆናል።

ኢትዮጵያውያን ሆነ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ከሁሉም በላይ ሠላም ይፈልጋሉ። ስለሠላም ያላቸው መሻት ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ጋር አብሮ ላለመኳዝ ካላቸው ቁርጠኝነት፤ ለዘመናት ድህነት እና ኋላቀርነት ከፈጠረባቸው ጠባቂነት እና የብሔራዊ ክብር መጓደል ለዘለቄታው ለመውጣት ካላቸው ብሔራዊ መነቃቃት የሚመነጭ ነው።

ልማት ከሕግ እና ከሞራል አኳያ የሚበረታታ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ፍላጎት ነው፤ ይህን ፍላጎታቸውን በአንድም ይሁን በሌላ፤ በግልጽ ይሁን በተለመደ የሴራ መንገድ ለማሰናከል የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት ሊወገዝ የሚገባ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች የመልማት መብት የሚፈታተን ነው።

በተለይም ታሪካዊዋ የኢትዮጵያ ጠላት የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችን የመልማት መሻት ተጨባጭ እንዳይሆን፤ አካባቢውን የግጭት እና ያለመረጋጋት ማዕከል ለማድረግ እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ የየትኛውም ሀገር እና ሕዝብ ፍላጎት የሚወክል አይደለም። የዚህ ተግባር ፈጻሚ ሀገር ሕዝብም ቢሆን ከዚህ የመንግሥቱ እኩይ ተግባር ሊያተርፍ የሚችለው አንዳች ነገር አይኖርም።

በዚህ መንገድ ተጠቃሚ እንሆናለን ብሎ ማሰብ ዓለም አቀፍ እውነታውንም ሆነ የአካባቢው ሀገራትን እውነተኛ ፍላጎት በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ፤ ዘላቂ ተጠቃሚነትን አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል ከዘመኑ አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ ከሚገዛበት ዓለም አቀፍ መርሕ በተቃርኖ መቆም ነው።

ኢትዮጵያውያን ግን እንደቀደሙት ዘመናት ለፍትሕ እና ለሉዓላዊነታቸው የሚከፈለውን የትኛውንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ፤ በተለይም በልማት ብልፅግናቸውን ተጨባጭ ለማድረግ የጀመሩት ትግል ብሔራዊ ክብራቸውን ምሉዕ የሚያደርግ በመሆኑ የሚጠይቃቸውን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፈል ከቀደሙት ዘመናት በተሻለ መልኩ ዝግጁ ናቸው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በዓላቶቻችንን በሕይወታችን ገልጠን እንኑርባቸው

**በቁምላቸው አበበ ይማም**
**(ሞሼ ዳያን )**
fenot1971@gmail.com

መስከረም ሽቅርቅር፣ ኩንስንስና ደማቅ ወር ነው። አዲስ መንፈስ ብርታት ጉልበት የሚያጋባ ኃይለኛ ወር ነው። ሜዳው ጋራ ሸንተረሩ በአደይ አበባ የሚደምቅበት፤ ክረምቱ ወጥቶ ዝናብ የሚቀንስበት፤ ወንዞች ጎለው ዘመድ ከባዳ የሚገናኝበት፤ እሸት የሚያሽትበት ተስፋ የሚጎመራበት ምትሐታዊ ወር ነው።

የዘመን አቆጣጠራችንን ከተፈጥሮ ጋር የሞሸረ ወር ነው። በእነዚህና በአያሌ ምክንያቶች መስከረምን እወደዋለሁ። በእንቁጣጣሽ 2017ን በአደይ ተቀብለን መስቀል ላይ ደርሰናል። በጋሞ-መስቀላ፣ በወላይታ-ጊፋታ፣ በሐድያ-ያሆዴን እያከበርን ነው። እሬቻም መጣሁ መጣሁ እያለን ነው።

እነዚህን በዓላት ጨምሮ ጥምቀትን፣ ገናን፣ ትንሳኤን፣ ኢድ አልፈጥርን ሆነ መውሊድን እና ሌሎች በዓላትን በአደባባይ በውጭ እናከብራቸዋለን እንጂ በቤታችን በውስጣችን አናከብራቸውም ብዬ አምናለሁ። በእውነት በሕይወታችን አንገልጣቸውም አንኖራቸውም። በዚህ የተነሳ ሙሉዕ አይሆኑልኝም። ሸንግለናቸው አታለናቸው ሸውደናቸው፣ አሹፈን ባቸው ተጠቃቅሰንባቸው፣ ተላልፈን፣ ወዘተረፈ የምናሳልፋቸው ስለሆነ ጥፋተኝነት ይሰማኛል።

ለነገሩ እራሳችንን ነው የምንሸውደውና የምና ታልለው። እንደ ሕዝብም እንደ ሀገርም ይህ ጥፋተኝነት ተሰምቶን እነዚህን የፍቅር የሠላም የይቅር ባይነት የትሑትነት የመስጠትና ራስን ዝቅ የማድረግ በዓላት በሕይወታችን ገልጠን ካልኖርናቸው ዓመት በመጣ በሄደ ቁጥር ብናከብራቸው ምን ትርጉም አለው። ስላቅና ምጸት ካልሆነ በስተቀር። እናም ዛሬም በድጋሚ እንኑራቸው በዕለት ተዕለት ሕይወታችን እንግለጣቸው እላለሁ። በዚህ አንድምታ ነው እንግዲህ እሬቻን በወካይነት የማነሳው።

እንኳን ለሁሉም በዓላት አደረሰን አደረሳችሁ! አሜን። ከዚህ በቀደመ መጣጥፌ ሦስቱ አብርሃማዊ ዕምነቶች ማለትም ክርስትና፣ እስልምና እና የአይሁድ ዕምነቶችን ከእነ በጎ ባሕላቸው በተለይ ልሒቃን ወይም ጉልህን ነን በምንል ዕቡያን ባለመገለጣቸው፣ በየዕለት ተዕለት ሕይወታችን ባለመታየታቸው፣ በተግባር ስላልኖርናቸው፣ ከዘመናዊው ትምህርት ጋር መሳ ለመሳ ስላላስኬድናቸው እንዲሁም ከምዕራብም ሆነ ከምሥራቅ እንዳሉ በገለበጥናቸው ርዕዮተ ዓለሞች ስለደፈቅናቸው ሀገራችንን ዛሬ ለምትገኝበት ሁለንተናዊ ቀውስ ተዳርጋለች።

ለዚህ ደግሞ ልሒቃን ተብዬዎች በአንድም በሌላ መልኩ ተጠያቂ ነን። በዛሬ መጣጥፌም ልሒቃንን በእርግጥ እሬቻን እንኖረዋለን በሕይወታችን እንተረጉመዋለን ስል እጠይቃለሁ። መቼም አፋችንን ሞልተን እንዴታ አንልም። ሀገራችን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ፀሐይ የሞቀው ዓለም ያወቀው የአደባባይ ሐቅ ነውና ።

በተፈጥሮዬ ጨለምተኛ የሚሉት አይነት ሰው አይደለሁም። ሆኖም ባሕላዊ ወረቶቻችንን መኖር በተግባር መግለጥ ካልጀመርን መጭው ጊዜ ከዚህ የከፋ እንደሚሆን እነግራችኋለሁ። ለዚህ ነው ቆም ብለን ከእያንዳንዳችን ዕምነትና ባህል አኳያ ራሳችንን ያለ ርኅራኄ መገምገምና መቤዠት የሚያስፈልገን። ለቀብድ ያህል ይሄን ካልሁ ወደ ገደለው።

ዓለም አቀፉ የእርቅ፣ የሠላም፣ የግልግልና የሽምግልና ረቡኒ (መምህር) ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ “የሠላምና ዕርቅ ትርጉምና መንገዶች” በሚለው ማለፊያ መጽሐፋቸው የሠላም የእርቅ አድማሶች በማለት በመጀመሪያ ሰው ከራሱ ጋር ከዚያ ከጎረቤቱ፤ ከማኅበረሰቡ ጋር በመጨረሻም ከተፈጥሮ ጋር እርቅ፤ ሠላም ማውረድ እንዳለበት ይተነትናሉ። ሰሞኑን የሚከበረው የእሬቻ በዓል ሰው በመጀመሪያ ከራሱ ጋር በመቀጠል ከጎረቤቱ ከዚያም ከተፈጥሮ ጋር የሚታረቅበት ማዕድ ነው።

> **እሬቻ ሠላም፣ ፍቅር፣ ይቅርታና አንድነት የሚፈፀምበት በመሆኑ አብሮነትን ስለሚያበረታታ አሰባሳቢ ነው**

እሬቻ ሠላም፣ ፍቅር፣ ይቅርታና አንድነት የሚፈፀምበት በመሆኑ አብሮነትን ስለሚያበረታታ አሰባሳቢ ነው። ጥልን ቂምን ጥላቻን እያራገፈ መልካም መልካሙን ማለትም ሠላምን ዕርቅን የሚያጠናክር ስለሆነ በውስጠ ታዋቂ ሠላምን ይዟል። የኦሮሞ ባሕልና ታሪክ ተመራማሪና ፀሐፊ አቦ ድርቢ ደምሴ እሬቻ ማለት ኦሮሞ ለምለም ሳርና አበባ ይዞ ፈጣሪን የሚያመሰግንበት ክዋኔ ሲሆን በሐይቅ፣ በወንዝ፣ በምንጭ ወይም በውሃ ዳርና በተራራ ብቻ የተወሰነ ግን አይደለም ይላሉ።

ልጅ ሲወለድ፣ አዲስ ቤት ሲሠራ፣ ሙሽራ ሲወጣ፣ በዘር ወቅትም፣ ወዘተረፈ እሬቻ ይደረጋል በማለት ከማኅበረሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ምን ያህል የተቆራኘ እንደሆነ ያስረዳሉ። የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑት አቦ ሙሉጌታ ደበበ (ፒ ኤች ዲ) በሌላ በኩል እሬቻ የገዳ ሥርዓት አንዱ አንጓ ነው ይላሉ። በማሳያነት ከሚጠቀሱት ዓበይት ምክንያቶች ቀዳሚው የሥርዓቱ ክዋኔ በቃሉና በአባ መልካ አጋፋሪነት መመራቱ ነው በማለት በዋቢነት ይጠቅሳሉ።

እሬቻ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚከወንና የመጀመሪያው በበልግ በተራራ ላይ አምላክን የሚያመሰግንበትና ዝናብ የሚለማመንበት ሲሆን ቱሉ እሬቻ ይሰኛል። አቦ ድርቢ ቱሉ እሬቻ መሬት አፏን ከፍታ የበልግ ዝናብን የምትጠብቅበት ወቅት ስለሆነ ፈጣሪን ዝናብ የሚለማመኑበት ጊዜ መሆኑን ይገልጻሉ። ለምለም ሳርና አበባ ተይዞ በሐይቅ፣ በወንዝ፣ በምንጭ ዳር የሚከበረው የምስጋና

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ሦስት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ ናቸው

## - ከማዕድን የወጪ ንግድ 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል


**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ሦስት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ መሆናቸውን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ። ከማዕድን የወጪ ንግድ 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱም ተገልጿል።

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የከበሩ ማዕድናት እና ግንባታ ግብዓት የሚሆኑ በርካታ ማዕድናት ያላት ሀገር ናት።እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶች አልምቶ ለመጠቀም ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

ከማዕድን ዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ ሦስት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ፕሮጀክቶቹ በአንድ ዓመት ከግማሽ ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ወደ ማምረት እንደሚገቡ ይጠበቃል ብለዋል።

አቶ ሚሊዮን፤ የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎቹ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ በዓመት ከ10 ቶን በላይ ተጨማሪ የወርቅ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ወደ ውጪ የሚላከውን የማዕድን ምርት በመጠንም ሆነ በጥራት እንዲጨምር እንደሚያደርገው ተናግረዋል።



ፕሮጀክቶቹ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ በጋምቤላና በትግራይ ክልሎች እንደሚገነቡ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በቤኒሻንጉል ክልል በኮርሙክ ወረዳ የሚገነባው ፕሮጀክት ትልቅና በዓመት እስከ ዘጠኝ ቶን ወርቅ የማምረት አቅም ያለው መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ሚሊዮን፤ ከሦስቱ ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ጉጂ የሚገኘው ነባር የወርቅ ማምረቻ ኩባንያ የማስፋፊያ ሥራ እየተሠራለት መሆኑን ገልጸው፤ ከወርቅ ባለፈም የፖታሽ ማዕድንን በአግባቡ ማምረት የሚያስችል ፕሮጀክቶች በአፋር ክልል እንደሚገነቡ ጠቁመዋል።

መንግሥት ባለፉት አምስት ዓመታት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ ዘርፉ ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ ማልማት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ወደ ውጪ ከተላኩ ማዕድናት 420 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በያዝነው አዲሱ በጀት ዓመትም 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑንም አንስተዋል።

የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች ዘርፉን እንዲያለሙ በሀገሪቱ ምቹ የሆነ አሠራር ተዘርግቷል። በዋናነት ከዘርፉ የውጭ ምንዛሬን በማግኘት የካፒታል ምንጭ እንዲሆን እየተሠራ ነው ብለዋል።

በተጨማሪ ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ማምረትና ለዜጎች የሥራ እድል መፍጠር በዘርፉ የሚሠሩ ሥራዎች መካከል መሆናቸውን ገልጸዋል።

# በምግብ ራስን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ አንድ ሀገር ሕዝቦችን ከአደጋ፣ ከረሀብና ከርዛት የሚወጡበትን መንገድ ካላዘጋጀ ሙሉ በሙሉ ሉዓላዊ ነው ለማለት አይቻልም። የምግብ ሉዓላዊነት የአንድ ሀገር ሉዓላዊነት መሠረታዊ አካል ነው።

የምግብ ሉዓላዊነት ስናነሳ የምግብ መብት የሚባል ነገር አለ። ይህ የአንድን ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ሕዝብ በልቶ የማደር መብት እንዳለው የሚገልጽ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ የራሷን የሆነን የግብርና እርሻ የፈጠረች ሀገር እንደመሆኗ መጠን የምግብ ሉአላዊነቷን ማረጋገጥ የግድ ይላል ነው ያሉት።

ይህን እውን ለማድረግም የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ የሥርዓተ ምግብ ሽግግር ተብሎ እየሠራ ያለው ሥራ ተጠቃሽ መሆኑን ያነሳሉ። ዘላቂነት ሌላኛው የምግብ ሉአላዊነት ማረጋገጫ መንገድ ነው። ይህም ኢትዮጵያ የምታመርተው የምግብ አይነትና መጠን ለሕዝቦቿ የሚዳረስ፤ የህብረተሰቡን የንጥረ ምግብ ፍላጎት መሠረት ያደረገና ዘላቂነት ያለው አሠራር መዘርጋትን ይጠይቃል ሲሉ ያብራራሉ።

የምግብ ሉአላዊነት ስንል ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ያለው መሆንም ይጠበቅበታል።ኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2015 ዓ.ም 17 የልማት ግቦች እና 169 ትልሞች የያዘውን ዘላቂ የልማት ግብ ተቀብላለች ያሉት ዶክተር ጌታቸው፤ መሠረታዊ እሳቤው ረሀብን ከዓለም ዙሪያ ማጥፋት ነው። ከዝቅተኛ ደረጃ ድህነት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማውጣት፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብና ሰላምንና ትብብርን የሚያጠናክር ነው። በራሷ በኩልም የ10 ዓመት የልማት ግቦችን ቀርጻ እየሠራች መሆኑን ጠቅሰዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የስንዴ ልማት፣ የሌማት ቱርፋትና አረንጓዴ አሻራን ጨምሮ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ በእነዚህ መርሃ ግብሮችም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተገኙ ነው። ለአብነትም ስንዴን ከውጭ ሀገር ከማስገባት በመላቀቅ በአንጻሩ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሉን ያነሳሉ። አነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግና ቴክኖሎጂን በስፋት እንዲጠቀም ለማድረግ የፋይናንስ አቅርቦት ትኩረት ተሰጥቶታል።የተመረተው ምግብም ተደራሽነትና ይዘት ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራትም ሕፃናት ላይ የሚስተዋለውን መቀንጨር ለማስቀረት በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት።

የምግብ ሉዓላዊነት ስለተመኘነው ብቻ አይመጣም የሚሉት ዶክተር ጌታቸው፤ በፌዴራል ደረጃ 14 ሚኒስትሮችን ያካተተ የምግብ ሥርዓት ሥነምግብ ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሠራ መሆኑን ያስታወሱት ዶክተር ጌታቸው፤ ይህም የሚያጋጥሙ ከፍተኛ ችግሮችን የሚፈታና አቅጣጫዎችንም ያስቀምጣል። በክልሎችም በተዋረድ እየተዋቀረ ሲሆን ያሉ ሀብቶችን ማቀናጀትና ማሰባሰብ ላይ ይሠራል።

የምግብ ሉዓላዊነት የሰብዓዊ ክብር ጥያቄን እንደሚያስከትል ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በሚያጋጥሙ ችግሮች ምክንያት በርካታ ዜጎች በምግብ እርዳታ ይኖራሉ። ይህ የምግብ እርዳታ በአብዛኛው ከውጭ ለጋሾች የሚመጣ ነው። ይህ ደግሞ ውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ ለመግባት እድል የሚፈጥር መሆኑን ነው ያስረዱት።

አንድን ሀገር የሚያስከብረው ወታደራዊ አቅሙ በአንድ በኩል የመንግሥት ጥንካሬና የሕዝቦች ደህንነት በልቶ አድሮ በሀገራቸው መኩራትም ጭምር ሲኖር መሆኑን ጠቅሰው፤ ብዙ ዜጎቻችን እርዳታ ላይ የሚመሠረቱ ከሆነ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሉዓላዊነትን ጥያቄ ውስጥ ማስገባቱ የማይቀር ነው። እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ይህንን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ያለሙ ናቸው።

የምግብ ሉዓላዊነት መንግሥት በሚሠራው ብቻ የሚረጋገጥ ስላልሆነ የግል ዘርፉ ፣ አርሶ አደሩና መላው ኢትዮጵያውያን ርብርብ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም እርዳታ የትም ሀገር ተለመደ መሆኑን አስታውሰው፤ ይሁን እንጂ እንደ ማህበራዊ ረድኤት ሆኖ መቀጠል የለበትም።

ስለሆነም ሁላችንም የምንወዳትን የሀገራችንን አንድነትና ሉዓላዊነት የሚፈታተን ኃይል ሆኖ የሚመጣ እድል መኖሩን ተገንዝበን የዜጎችን ክብር ለማስጠበቅና የሀገራችንን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ መሥራት ይኖርብናል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃና ዘላቂ ልማት ፕሮፌሰሩ በላይ ስማኔ በበኩላቸው፤ የምግብ ሉዓላዊነት አለማረጋገጥ ብዙ ፖለቲካና የፋይናንስ ጫና ያስከትላል። ምክንያቱም የምግብ ሉዓላዊነት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በበቂ ሁኔታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በሀገር ውስጥ አምርቶ ማቅረብና ራስን መቻል ማለት ነው ይላሉ።

በብዙ የሀገራችን ፖሊሲዎች፣ በግብርና ሰነዶች እና በሌሎችም ጉዳዮች ውስጥ የምግብ ዋስትና ቁልፍ ሀገራዊ ሥራ መሆኑ ይገለጻል። በእርሻ ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን ማሻሻል፣ በቴክሎጂ አቅርቦትና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን በወቅቱ ከማቅረብ አንጻር የተለያዩ ሥራዎች ይሠራሉ። ብዙ ለውጦችም ተመዝግበዋል።

ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አኳያም በጥራጥሬ፣ በሰብል፣ በእንስሳት ልማት ዘርፎች ለውጦች አሉ። ነገር ግን ይህ ለውጥ ካለው የሕዝብ ቁጥር አኳያ በበቂ ሁኔታ የኢትዮጵያን የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ እንዳልቻለ ይገልጻሉ።

የአየር ንብረት ለውጥን፣ የሕዝብ ብዛታችንም እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ማስፈን አለመቻል የምግብ ዋስትናን እንዳናረጋግጥ መሰናክል ፈጥሮብናል የሚሉት ፕሮፌሰር በላይ፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ግብርና ብቻ በቂ አይደለም የሚባለውም ለዚህ ነው። በመሆኑም በጤና፣ በቤተሰብ ምጣኔና በሌሎችም መስኮች ላይም ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው ያመለክታሉ።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ጦርነትና ግጭቶች የሚያስከትሉት የማህበራዊ አለመረጋጋት የምግብ ዋስትናችንን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶታል የሚሉት ምሁሩ፤ ከዚህም በተጨማሪ የዩክሬንና የሩስያ ጦርነት እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚስተዋሉ ችግሮች የራሳቸውን አሉታዊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ይላሉ።

አብዛኞቹ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች ከውጭ የሚመጡ ናቸው። ይህ ደግሞ ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በተገናኘ የሚያጋጥም ሌላኛው እንቅፋት ነው።በጥቅሉ ምንም እንኳን ሰፊ ጥረት ቢደረግም አሁንም ድረስ ሙሉ በሙሉ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ አልተቻለም ነው ያሉት።

የተቀረጹ ፖሊሲዎችን ለመተግበር ብዙ ርቀት መሄድ ይኖርብናል። ከዚህ ውስጥ የሚጠቀሰው ማህበረሰብን ያማከለ ፖሊሲ ማውጣትና አስተዳደራችንን ማዘመን እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ከዚህ በተጨማሪ ምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በስነምህዳርና በግብርና ሥርዓት የተማከሉ ቴክኖሎጂዎችን በብዛት እንዲያፈልቁ መሥራት ያስፈልጋል። የኤክስቴንሽን ሥራውን ከፖለቲካ ሥራው መለየትና ግብርናን ማዘመን ላይ ሙሉ ጊዜውን የሚያውል የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ እንዲኖር መሥራት ይገባል።

አርሶና አርብቶ አደሮች ያላቸውን ሀብት በአግባቡ እንዲጠብቁና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ የግል ዘርፉ በግብርናው ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በስፋት እንዲጠቀም ማድረግም ያስፈልጋል። አጋር አካላት የሚሰጡትን ድጋፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይጠበቃል።

መሥራት ያለብንን የቤት ሥራ በአግባቡ ከሠራን ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፋ የምግብ ሉዓላዊነቷን ማስጠበቅ የሚያስችል አቅም እንዳላት ጠቁመው፤ ሰላም ማስጠበቅ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚያከናውኑትን ሥራ በአግባቡ መከታተልና መቆጣጠር ላይም ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በምግብ ራስን ለመቻል ብሎም የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እየሠራች ነው።ይሁን እንጂ ሀገራዊ ሰላምን ማስፈን፣ አሠራርና አስተዳደርን ማዘመን ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል።ለዚህ መሳካት ደግሞ መንግሥት የሚያደርገው ጥረት በቂ ስላልሆነ ሁሉም ባለድርሻዎች በትብብር መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸው ይሰጣሉ።

# የባህር በር እጦት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንጂ የባህር በር አለመኖሩ በሎጂስቲክስ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ የገሃዱ ዓለም እውነታ ነው።

የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ወቅታዊና የሎጂስቲክስ አቅምን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ በብዙኃኑ ዘንድ ሲገለጽ ቆይቷል። የባህር በር አለመኖር በተለይ ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸው ሆነ ወደ ሀገር የምታስገባቸውን ዕቃዎች ደህንነታቸውና ምስጢራዊነታቸው ተጠብቆ በፍጥነት ከመላክና ከማስገባት አንጻር ከፍተኛ ጫና የሚፈጥርም ነው።

በተጨማሪም እቃዎች በሚገቡና በሚወጡበት ወቅት በወደብ የሚኖራቸው ቆይታ ከፍተኛ ወጪ እንዳለው እና ይህም የዋጋ ንረት እንዲከሰት የሚያደርግ ነው። የባህር በር ያላቸው ሀገራት የባህር በር ከሌላቸው ሀገራት የበለጠ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሉዓላዊነታቸው የሚያረጋግጡባቸው ሰፋፊ እድሎች እንዳሏቸው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ(ዶ/ር) ለኢፕድ በሰጡት ቃለ ምልልስ፤ የባህር በር ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ የሆነ ዐቢይ ጉዳይ ነው ያላሉ። የባህር በር በበርካቶች ዘንድ ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ቢሆንም በተለይ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ሰፋ ያለ ግምት የሚሰጠው ነውም ባይ ናቸው።

ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ባለመሆኗ ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ፣ ለወጪና ገቢ ንግድ መቀዛቀዝ እንዲሁም ለተለያዩ የደህንነት ስጋቶች ተጋልጣለች የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤በተጨማሪም በባህር አካባቢ የሚገኙ ጥቅሞች ማለትም የአሣ እና የተለያዩ የማዕድናት ምርት ማጣቷን ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ የባህር በር ባለቤት አለመሆን ከኢኮኖሚው ጉዳት በተጨማሪ የሀገር ሉዓላዊነትና ደህንነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት ነው። በተለይ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ትልቁ የመርከብ ድርጅት ያላት ሀገር በመሆኗ እነዚህ መርከቦች በሰላም የእለት ተዕለት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸው ጠንካራ የባህር ኃይል ለመገንባት የባህር በር ያስፈልጋል።

በባህር በር አካባቢ ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ልማቶች፣ ኢኮኖሚክ ዞን እንዲገነቡ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት እንዲያድግ በማገዝ የሥራ እድል ፈጠራ፣ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲሁም በሀገር የሚመረቱ ምርቶች እሴት ጨምሮ ለመላክ እድል እንደሚፈጥር ያብራራሉ። በባህር በር ችግር ምክንያት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው ምርቶች 78 በመቶ በላይ የሚሆኑት በጥሬው የሚላኩት መሆናቸውን ያስረዳሉ።

የባህር በር የሌላቸው ሀገራት ካላቸው ሀገራት በላይ በኢኮኖሚው የበለጠ ተጎጂ መሆናቸው እሙን ቢሆንም የተለያዩ ፖሊሲዎቻቸው በመሻሻላቸው ወደብ ሳይኖራቸው የኢኮኖሚ ሉዓላዊነታቸውን ያረጋገጡ ሀገራት አሉ ያሉት ደግሞ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና ፓን አፍሪካ ንግድ ምክር ቤት ዋና ኃላፊ ክቡር ገና ናቸው።

በዓለም ከ40 በላይ የሚሆኑ ሀገራት ወደብ የላቸውም የሚሉት ክቡር ገና፤ ወደብ ሳይኖራቸው የተሻለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና እድገት በማምጣት ተጨባጭ ውጤት ያሳዩ ሀገራት እንዳሉ ይጠቁማሉ።

የተለያዩ እቃዎች፣ ሸቀጦች በመቀበልና በመላክ ሂደት ውስጥ ያለው የጉምሩክ፣ የታክስ፣ እንዲሁም በኬላዎች ላይ ያለው ቢሮክራሲ እንዲሁም የተጋነነ ቀረጥ ማቃለል ለነገ የማይባል ውሳኔ የሚፈልግ ነውም ባይ ናቸው።

እነዚህም በምርታማነትም ላይ ሆነ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የተወዳዳሪነት አቅም እንዳይጎለብት የሚያደርጉ መሆናቸውን ያመላክታሉ።

የባህር በር ሳይኖራቸው ኢኮኖሚ ልማታቸው ካሳደጉ ሀገራት ተሞክሮ መውሰድ ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን፤ ሉክተንበርግ፣ካዛኪስታን፣ ሞንጎሊያ፣ ቦትስዋና የባህር በር ባይኖራቸውም ራሳቸውን አደራጅተው ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት ወደብ ካላቸው ሀገራት እኩል መሆን ከቻሉ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

ይህ ማለት ግን የባህር በር መኖር የኢኮኖሚ ዕድገት አያመጣም ሳይሆን በባህር በር ብቻ ላይ ማተኮር ተገቢ አለመሆኑን ለመግለጽ መሆኑን ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ የባህር በር ሳይኖራት 10 በመቶ ያደገችበት ወቅት አለ የሚሉት ክቡር ገና፤ የባህር በር ፍላጎቱ እንዳለ ሆኖ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ስብራት ለመጠገን አሁን በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋለው ግጭት ማቆም፣ በየዘርፉ ውስንነት ያለባቸው ፖሊሲዎችና የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚወስድ የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም፣ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን ማሳደግ እንዲሁም ቱሪስትን በብዛት መሳብም ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ከባህር በር በተጨማሪ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው የጠቀሱት።

# “የለሚ የሲሚንቶ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ትውልድ ድህነትን እንደማይወርስ ይልቁንም ለእድገት እና ብልጽግና ጥሩ መደላድል እንደሚጠብቀው እንደሚያሳይም ገልጸዋል።

እንደ ለሚ ያሉትን የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች በመላው ሀገራችን ካባዛን በሥራ ፈጠራ እና በሀገራዊ እድገት ላይ የሚኖረው የመባዛት ፍሬ አቻ የማይገኝለት እንደሚሆን አመልክተው፤ በተለይም በብረት ምርት፣ በማዳበሪያ ምርት ብሎም በሰፊው የኢንዱስትሪ እና ግብርና ልማት አብዮት የሚኖረው ተፅዕኖ ሰፊ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ትልቅ ሀገራትን የሚገዳደሩ ፈተናዎች ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው መፍትሔዎችን እንደሚሹ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አመልክተው፤ በመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ የሚኖር የጋራ ትብብር እምቅ ሀብትና እድሎችን ለመጠቀም ብሎም ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ቁልፍ ነው። በመሰል ሥራዎች ላይ ኢንቬስት በማድረግ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ማሻሻል እንዲሁም ክብር ያለው አኗኗር እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚቻል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የለሚ ብሔራዊ የሲሚንቶ ፋብሪካ በ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር በጀት ተይዞለት የተገነባ መሆኑ ታውቋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በዓላቶቻችንን በሕይወታችን ገልጠን. . .

**ከገጽ 3 የዞረ**

በዓል ደግሞ መልካ እሬቻ በመባል እንደሚታወቅ አቦ ሙሉጌታ ያብራራሉ።

ፈጣሪ ዝናብ ስለሰጠ ከክረምት ወደ ብራ ስለ አሸጋገረ የሚመሰገንበት እንዲሁም አዝመራው ደርሶ ተሰብስቦ ወደ ጎተራ እንዲገባ የሚለመንበት መሆኑን አክለው ይገልጻሉ። በፕሮፌሰር የሠላም አድማስ እይታ መሠረት እሬቻ ሦስቱንም የሠላም አለባውያን በአንድነት የያዘ የእርቅ፣ የሠላም ገበታ ነው ማለት ይቻላል። ጥያቄው እየኖርናቸው ነው ወይ!? የሚለው ነው። ለማንኛውም ሦስቱን የሠላም አድማሶች ከእሬቻ እሴቶች አንጻር አንድ በአንድ እናመሳክር፡-

**1ኛ . ከራስ ጋር ሠላም ፤**

ዓለም አቀፍ አሸማጋይ እና የሠላም አባት ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ ከፍ ብሎ በጠቀስሁት መጽሐፋቸው ገጽ–102 ላይ “ውስጣዊና መንፈሳዊ ሠላም ከራስ ጋር ሠላም ማውረድ፣ መታረቅ ነው። ከፈጣሪ ጋር ሠላም ከማውረድ ጋር ትስስር አለው። ውስጣዊ ሠላም ከሌሎች ጋር ለሚመሠረት ሠላም ወሳኝ ነው። ውስጣዊ ሠላም ያለው ሰው ምን ያህል ከሌሎች ጋር በሠላም እንደሚኖር እና ሠላም እንደሚያካፍል ይታወቃል። ውስጣዊ ሠላም ያላቸው ሰዎች አስታራቂና ሠላም ገንቢም ናቸው። ሠላማቸው ወደሌሎች ይፈሳል። ከራሱ ጋር የታረቀና ውስጣዊ ሠላም ያለው ሰው የሕይወትን መስተጋብር የተገነዘበ ስለሆነ ከማኅበረሰቡና ከተፈጥሮ ጋርም ሠላምና እርቅን ያወረደ ነው። ከራስ ጋር የሚፈጠር ሠላም ለሠላም አድማሶች መነሻም ውጤትም ነው። ...”

እሬቻ ከመደረጉ በፊት ከራሱ ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር የተቀያየመ የተጋጨ ካለ እንዲወጣ ሽማግሌዎች በኦሮምኛ “እውነትን ከአምላክ ፆታን ከምድር መደበቅ አይቻልም። በውሻም ሆነ በልጅ ምክንያት የተጋጨ ካለ ከፈጣሪ ጋር እንዳያቀያይመን ይውጣ” በማለት እንደሚያግባቡ ይህን ሳያደርጉ ቢቀሩ ደግሞ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንደሚያስወቅሳቸው አቦ ድርቢ ያስረዳሉ። የሀገር ሽማግሌዎች ቢያንስ በመጋቢትና በመስከረም በዓመት ሁለት ጊዜ እርቅ የማውረድ የመሸምገል አጋጣሚ እንዳላቸው ይገልጻሉ። ሰሞኑን የሚከበረው መልካ እሬቻም ሆነ በወርሐ መጋቢት የሚከበረው ቱሉ እሬቻ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ከራስ ጋር መታረቅ ሠላም ማውረድ ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነና በዓሉ ቤትን ራስን በእርቅ የማፅዳት፤ የጥል ግድግዳን የማፍረስና ፋይል ዘግቶ ወደ አዲስ ምዕራፍ የመሻገሪያ ድልድይ መሆኑን አቦ ሙሉጌታ አክለው ያብራራሉ።

**2ኛ . ማኅበራዊ ሠላም፤**

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ ስለ ሁለተኛው የሠላም አድማስ ገጽ– 103 ላይ “ማኅበራዊ ሠላም ከራስ ጋርና ከተፈጥሮ ጋር ከሚደረግ ሠላም ጋር ጥብቅ ትስስር አለው። ይህ ማለት ግን ማኅበራዊ ሠላም ከሌለ ውስጣዊ ሠላም አይኖርም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም። ሆኖም ብጥብጥና ሁከት ባለበት ውስጣዊ ሠላምን ማስፈንንም ሆነ ማስቀጠልን ፈታኝ አያደርገውም ማለት አይደለም። ሌላው ማኅበራዊ ሠላም ከተፈጥሮ ጋር ከሚደረገው ሠላም ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው መሆኑን መገንዘብ ነው። ግጭትና ጦርነት በተደጋጋሚ የተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ስለሚጎዳ ደኑም ስለሚጨፈጨፍ አካባቢው ይራቆታል። በዚህም ሥነ ምሕዳሩ ስለሚዛባ የከባቢ አየር ለውጥን ያስከትላል። ለዚህ ነው የማኅበራዊ ሠላም መኖር ለፍጥረትና ለአካባቢ ጥበቃ ዋስትና ተደርጎ የሚወሰደው።

“ውስጣዊና መንፈሳዊ ሠላም ከራስ ጋር ሠላም ማውረድ፣ መታረቅ ነው:: ከፈጣሪ ጋር ሠላም ከማውረድ ጋር ትስስር አለው:: ውስጣዊ ሠላም ከሌሎች ጋር ለሚመሠረት ሠላም ወሳኝ ነው:: ውስጣዊ ሠላም ያለው ሰው ምን ያህል ከሌሎች ጋር በሠላም እንደሚኖር እና ሠላም እንደሚያካፍል ይታወቃል

“ፕሮፌሰር እንደሚሉት ከራስ ጋር የሚፈጠር ውስጣዊ ሠላም ከጎረቤትና ከማኅበረሰብ ጋር የሚደረግ እርቅ መሠረት ነው። በእሬቻ ለመታደም ከራስ ጋር መታረቅ ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ከራሱ ጋር ሠላም ያለው ደግሞ ከጎረቤቱ ጋር የመጋጨት አጋጣሚው ዝቅተኛ ነው።

ሆኖም ከጎረቤቱ ጋር ወይም ከሌላ ሰው ጋር ግጭት ቢፈጠር የሀገር ሽማግሌዎች በቱሉ ወይም በመልካ እሬቻ የማስታረቅ መልካም አጋጣሚም ኃላፊነትም ስላለባቸው ማኅበራዊ ሠላምን ከመታወክ ይታደጉታል። ለዚህ ነው የሥነ ማኅበረሰብ አጥኚዎች መጀመሪያ ከራስ በመቀጠል ከጎረቤት ጋር የሚፈጠር ሠላም ከተፈጥሮ ጋር ለሚደረስ ሠላም መደላድል እንደሆነ የሚያስረዱት። ታላቁ መጽሐፍስ “እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።” አይደል የሚለው! ?

**3ኛ . የተፈጥሮ ሠላም፤**

ፕሮፌሰር በገጽ–104 ላይ “የተፈጥሮ ሠላም ከማኅበራዊ እና ከውስጣዊ ሠላም ጋር ጥብቅ ትስስር አለው። ከተፈጥሮ ጋር ሠላም፣ እርቅ ማውረድ አካላችን ከታነፀበት ምድር ጋርም መታረቅ ነው። ከተፈጥሮ፣ ከዩኒቨርስ ሥርዓትና ኃይል ጋር መንሰላሰል የውስጣዊ ሠላም ምንጭ ነው። ...የተፈጥሮ ፍቅርና እንክብካቤ ለማኅበራዊ ሠላም መስፈን የማይተካ ሚና እንዳለው የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

“እሬቻ ከሁለቱ የሠላም አድማሶች ይልቅ ከተፈጥሮ ጋር ለሚደረግ እርቅ ያደላል ቢባል ማጋነን አይሆንም። በቱሉ እሬቻ ፈጣሪውን ለበልግ እርሻ፣ ለከብቶች ግጦሽና ለውሃ ዝናብ የሚለምንበት መሆኑ መልካ እሬቻው ደግሞ ፈጣሪው ዝናብ ስለሰጠው፣ ከክረምት ወደ ብራ ስላሸጋገረው የሚያመሰግንበት በሌላ በኩል ያልተሰበሰበውን እህል በአደራ የሚሰጥበት የአምላክን ጥበቃ የሚለማመንበት መሆኑ በተለይ ለምለም ሳርና አበባ ይዞ ውሃ ዳር ፈጣሪ የሚመሰገንበት መሆኑ ከተፈጥሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን ያሳያል።

ይሁንና እሬቻ ደረጃው፣ ስፋቱ፣ ጥልቀቱ በየሠላም አድማሱ የተለያየ ቢሆንም ሰው ከራሱ፣ ከጎረቤቱ በመጨረሻም ከተፈጥሮ ጋር በአንድ የእርቅ፣ የሠላም፣ የመቀባበል፣ ወዘተ . ማዕድ ቀርቦ የሚቋደስበት ስለመሆኑ አያጠያይቅም።

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ”...በተለያዩ ማኅበረሰቦች ሀገር ግንባታ Nation Building በመሐላቸው ያለውን ልዩነት አጥብቦ ግድግዳዎችን አፍርሶ የጋራ ማንነት መገንባት ነው። ...” ይላሉ። የሀገር በቀል እውቀቶችና የባሕል ተመራማሪው አቶ አብዱልፈታህ አብደላ ይሄን የፕሮፌሰር ሀሳብ ይጋራሉ።

በዓሉ በአዲስ አበባ ሌሎችን የማኅበረሰብ ክፍሎች ባሳተፈ አግባብ መከበሩ ለሀገረ ግንባታ መሠረት ጥሏል ማለት ይቻላል ሲሉ ዘላቂ ፋይዳውን ያመላክታሉ። የጋራ የሆኑ እሴቶችን ባሕሎችን እያጎለበትን እያሳደገን በሄድን ቁጥር መተዋወቅ፤ መከባበር፤ መቀባበል ስለሚጨምር እኔነት በእኛነት እየተተካ ስለሚሄድ ለሀገርም ሆነ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ እርሾ እንደሚሆን ተመራማሪው ያስረዳሉ።

ዛሬ ከምንገኝበት መንታ መንገድ ላይ የደረስነው ባሕሎቻችንን እሴቶቻችንን ለሀገረ መንግሥትም ሆነ ለሀገር ግንባታ ባለማዋላችን ነው ሲሉ አቶ አብዱልፈታህ ይሞግታሉ። አቦ ሙሉጌታ በበኩላቸው እንደ ዓድዋ ያሉ የድል በዓሎቻችን፣ እሬቻ፣ ሻደይ፣ አሸንዳ፣ ፍቼ ጨምበላላ፣ ጊፋታ፣ ወዘተረፈ አንድ የሚያደርጉን ባሕሎች በበዙ ቁጥር ኢትዮጵያዊነታችን ይጠናከራል። ከተገኘንበት ብሔር ይልቅ ኢትዮጵያዊነታችን እየገዘፈ ይሄዳል። እየተዋሓድን፣ እየተቀባበልን፣ እየተከባበርን በሄድን ቁጥር እየተዋደድን እንሄዳለን አንድነታችንም በዚያው ልክ ይጎለብታል ሲሉ ይጠቁማሉ።

**እንደ መውጫ**

መስቀልንም ሆነ እሬቻም ወይም ጊፋታ፣ መስቀላዮም ሆነ ፍቼ ጨምበላላ አሸንዳ ሻደይም ሆነ ሶለል፣ ወዘተረፈ ሲከበሩ በተቻለ መጠን ከፖለቲካዊ አንድምታ ጋር ላለማቆራኘት ጥረት ሊደረግ ይገባል። በተወጠረች ፖለቲካዊ ገመድ በጥበብ በማስተዋል መጓዝ ግድ ይለናል። እሴቶቻችን ባሕሎቻችን በራሳቸው ሙሉ፣ ጮኸው የሚናገሩ፣ ከሩቅ እንደ ቀስተ ዳመና ደምቀው የሚታዩ ስለሆኑ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ማጋጌጫ አያሻቸውም። ቱባ መሆናቸው በራሱ ሙሉዕ አድርጓቸዋልና። አቶ አብዱልፈታህ እሬቻ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ይዞልን የሚመለሰው ምስጋናን፣ ይቅርታን፣ ሠላምንና አንድነትን እንጂ ሌላ አጀንዳን ሊሆን አይገባም ይላሉ።

ሆኖም የክልል ሰንደቅ ዓላማ እና የፓርቲ ዓርማ በማንገብ ፖለቲካዊ ቡልኮ መደረቡ ተገቢ አይደለም። ይህ ከእሬቻም ሆነ ከሌሎች በዓላት እሴቶች ጋር የሚጣረስ ከመሆኑ ባሻገር አቃፊነቱ ላይ ጥያቄ፣ ብዥታ፣ ግርታ ሊያስነሳ ይችላል። ከባሕላዊ፣ እሴታዊ አንድምታው ይልቅ ፖለቲካዊ ቱማታው ላይ ጊዜያዊ ነጥብ ለማስመዝገብ የሚደረግ መሸሎክሎክ ፊት ሊነሳ ይገባል።

ከሀገራዊ፣ ከቀጣናዊ፣ ከአሕጉራዊና ከዓለም አቀፋዊ ስትራቴጂና ሕልማችን አንጻር አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ሃይማኖትንና በዓላትን ለአማኙና ለተከታዩ መተው ሊበረታታ ይገባል። በነገራችን ላይ ሃይማኖትንና ባሕልን ከፖለቲካ ጋር የማጣቀስ አባዜያችን ትናንት የተጀመረ አይደለም። የዋለ ያደረ አባዜ እንጂ። ይህ ቅርሻ በዜጎች መካከል መጠራጠርን፣ ልዩነትን የሚያነብር ስለሆነ ሰከን ብሎ ማሰብ ይገባል። ለብሽሽቅ፣ ለእልህ ፖለቲካ በር እንዳይከፍት ጥንቃቄ ማድረግም ያስፈልጋል።

ከሁሉም በላይ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ላልገነባች ሀገርና ሕዝብ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት Political Correctness የልብ ትርታዋ ሊሆን በተገባ። ሆኖም በገዥው ፓርቲም ሆነ በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአፍ ወለምታ፣ ግራ ቀኙን ካለማመዛዘን፣ የመራጭን constituency ቀልብ ለመግዛት፣ “የአንቂን” Activist ቡራኬ ለማግኘት የሚፈፀሙ ፖለቲካዊ ስህተቶች ሀገርን ያልተገባ ዋጋ ሲያስከፍሉዋት ኖረዋል።

አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን ለጭብጨባ ተሚጋች ነን ባዮች ለሰብስክራይብና ለላይክ ሲሉ በስሜት ከመጋለብ ዛሬም ራሳቸውን በልጓም፣ በልባብ ሊገቱ ይገባል። ቢዘገይም አልረፈደም። ወደ መነጋገሪያው ቀርቦ አንደበትን ከመክፈት በፊት ሁለት ሦስቴ ማሰብና ከስሜታዊነት መታቀብ ያስፈልጋል። ገና ብዙ ያልተሻገርናቸው ሸለቆዎች፣ ገደሎች አሉብንና በእንቅርት ላይ ... እንዳይሆን አበክረን ልንጠነቀቅ ይገባል ።

ከጊዜያዊ ድል ዘላቂውን የሀገርና የሕዝብ ጥቅም ማስቀድም ትልቁን የተስፋ ስዕል አሻግሮ ማየት ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ እሬቻንም ሆነ መስቀልን በዓመት አንድ ጊዜ በአደባባይ ማክበር ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ኑሯችን እንተርጉማቸው። እንኑራቸው። በልካቸው እንገኝ። ልካቸው ሠላም፣ እርቅ ፣ ይቅርታ፣ መቀባበል፣ መግባባት፣ አብሮነት፣ አንድነትና ሰው ሆኖ መገኘት ነውና።

**ፈጣሪ የከርሞ ሰው ይበለን ! ሻሎም !**

**አሜን።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## “የአንጪቆረሩ” ፈርጥ

አስመረት ብሥራት

**ስመግቢያ ያህል**

አንጪቆረር ሲባል ሁልጊዜ በአዕምሮዬ የሚመጣው የሆነ ሩቅና አስፈሪ ስፍራ ነው፡፡ ከዛ አስፈሪ ቦታ ሰው በቅሎ በበጎነት መድረክ ተሸለመ ሲባል አንጪቆረር የሀገር ስም ነው እንዴ ብዬ ጠየኩ። ከሀገርም ሀገር መሆኑን ስረዳ አንጪቆረር በሰሜን ሸዋ በሲያደብርና ዋዩ ወረዳ ከደነባ 12ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ታዳጊ ከተማ መሆኗን ተረድቼ ለእናንተም ላካፍላችሁ ወደደኩ።

ይህች ከተማ እና በዙሪያዋ ትርፍ አምራች አርሶ አደሮች ያሉባት፣ በገበያዋ እንቅስቃሴም የተሻለች ከተማ ስትሆን በመሠረተ ልማት ከደነባ፣ ከሞረትና ጅሩ ወረዳ ዋና ከተማ ከእነዋሪ የሚያገናኝ መንገድም ያላት ከተማነች፡፡

አንጪቆረር ከተማ ከ1532 ዓ.ም በፊት የንግድ ማዕከል ሆና ስታገለግል ነበር የሚሉ ሀሳቦችም አሉ። ከ1532 ዓ.ም ወዲህ ባስኬቶ የሚባል ግለሰብ ጦርም አስፍሮባት እንደነበር ምሑራን ይናገራሉ። ከተማዋ መቼ እና በማን እንደተቆረቆረች እስከአሁን አሳማኝ መረጃ አለኝ የሚል አልተገኘም።

እግር ጥሎት ወደዚህች ከተማ ጎራ ካሉ በስንዴና ጤፍ ምርት ገበያዋ ተጨናንቆ ታገኟታላችሁ፡፡ በበሬ የሥጋ ቁርጥም ቀላል የምትባል ከተማ አይደለችም፡፡

ከዚህ ቀደም ስለአንጪቆረር ትርጉም ለማስረዳት የወረዳው ባሕልና ቱሪዝም እንዲሁም ብዙ ግለሰቦችና መጽሔቶች አራት ማስረጃዎችን በማቅርብ ለማስረዳት ጥረት ሲያደረጉም ቆይተዋል። እነዘህ ማስረጃዎች፤ 1ኛ በግራኝ መሐመድ ዘመን በራሱ በግራኝ መሐመድ አማካኝነት ስያሜው እንደተሰጣት ይነገራል። ሆኖም ይህ ብዙም ውሃ የሚቋጥር አይደለም፡፡ 2ኛው የጎንደር ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አፄፋሲል የአዳም ዘር የምትባል ሴት ልጅ ነበረቻቸው፡፡ ወደዚህ ቦታ መጥታ በመቅረቷ “አንቺው ቀረሽ” እየተባለች ለረጅም ጊዜያት ስትጠራ ከቆየች በኋላ በጊዜ ሂደት አንጪቆረር ወደሚል መጠሪያ እንደተለወጠችም ይነገራል፡፡ 3ኛው ደግሞ ጤፍ ሲታጨድ የሚቀረው ቃርሚያ ቆረን ይባል ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ የመሬቱ ባለቤት አንቺ ቆረን የሚል መጠሪያ እንደሰጡትም ይነገራል፡፡ በ4ኛ. ደረጃ ጠላ ቤት ስለነበረ ጠላ ሻጯን አንጪ ጠላውን ቆረር አድርገሽ በማለት ሰዎች ያዟታል፤ በዚህም የተነሳ አንጪቆረር እንደተባለ የሚያመላክቱ መላ ምቶች መኖራቸው ይነገራል።

ይሁን እንጂ ሁሉም መላምቶችና አፋዊ ታሪኮች እስካሁን የሰነድ ማስረጃ እንደሌላቸው ያስረዳሉ፡፡ አፈታሪኮች አንድ የታሪክ ማስረጃ መሆናቸው ምንም እንኳ ባይታበልም ትክክለኛ እና እውነተኛ ናቸው ብሎ ለመናገር ግን ጉልበት ያንሳቸዋል፡፡ በሰነድ ቢደገፉ ግን የተሻለ የማስረዳት አቅም ይኖራቸዋል በማለት ከሰነድ መረጃ ፈልገናል፡፡

ታዲያ ስለአንጨቆረር ሰነድ ላይ የት እናገኛለን? ከተባለ በሰነድ ላይ ስለአንጪቆረር ሰፍሮ የምናገኘው "የጥላሁን ብረሃንሥላሴ” የታሪክ መጽሐፍ ገፅ 10 ላይ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ አንጪቆረር የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በ19ኛው ክፍለ ዘመን /1806 እስከ 1840/ዓ.ም ዘመን በዘመነ ንጉሥ ሣሕለሥላሴ ሸዋን በሚያስተዳድሩበት ዘመን ነበር፡፡ በወቅቱ ምንም እንኳን የዛሬዋን የሲያደብረና ዋዩ ወረዳ የምትገኘዋን አንጪቆረር ታዳጊ ከተማ ባያስተዳድሯትም ንጉሥ ሳሕለሥላሴ የሸዋ ዝነኛና ታዋቂ ስለነበሩ “በሸዋ የነበሩት ባላባቶች ዝነኛ መሆን ጀምረው ስለነበረ አማርኛ ቋንቋ ውስጥም አንዳንዶቹ ስም መደባለቅ ጀምረው በሸዋ አማርኛ የሚከተሉትን ዘይቤዎች ተለመዱ፡፡

ሩቅ ለማለት----------አንጪቆረር፤

ታች ለማለት----------እንጦሮጦስ፤

ጥንት ለማለት---------የስብስቴ ጊዜ፤ ድሮ ለማለት------የአምኃየስ ጊዜ” እያሉ እንደተሰየሙ ያስረዳናል፡፡

ከዚህ በላይ ባጭሩ በተገለጸችውና በልምላሜዋ በታወቀችው በሰሜን ሸዋ አስተዳደር ልዩ ስሙ አንጪቆረር የተባለ ስፍራ በ1949 ዓ.ም ነው እንግዲህ ደረጄ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) የተወለዱት። እኛም እኚህን ምሑርና የበጎ ሰው ሽልማት የማኅበራዊ ጥናት ዘርፍ ተሸላሚ የዛሬ የሕይወት ገጽታ ዓምዳችን እንግዳ ያደረግናቸው።

1(ስለ አንጪቆረር አመሠራረት አንዱ አፈ ታሪክ ከግራኝ አሕመድ ወረራ ቀጥሎ በተደረገው የኦሮሞ ፍልሰት/መስፋፋት ምክንያት የዋዩን አካባቢ ያስተዳድር የነበረው የዋዩ የተባለ መሪ ነበር በእርሱ ስር ደግሞ ቦኪሳ የሚባል ጭፍራ አለ፡፡ የአንጪቆረር ገበያን የመሠረተውም ቦኪሳ ነው፡፡ የኛ ወላጆች ገበያውን የቦኪሳ ገበያ አድባሯንም የቦኪሳ አድባር ይሉ ነበር፡ )

**ልጅነት**

ደረጀ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) በ1949 ዓ.ም ነው አንጪቆረር ላይ የተወለዱት። ለትንሽ ጊዜ የቄስ ትምህርትን ተምረው የተወሰኑ ፊደሎችን ከለዩ በኋላ ነበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸው በዋዩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀመሩ።

ጋሽ ደረጀ የአስኳላን ደጅ ከረገጡ በኋላ ትምህርት ቤት መሄድ ጠልተው የአንድ ዘመዳቸው እርሻ ውስጥ ተኝተው ውለው እንደተማረ ሰው ከተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው ቤት መግባት ጀመሩ። “ይህ ልጅ እየተማረ ሳይሆን እርሻ ውስጥ ተኝቶ ነው የሚውለው ለምንድን ነው? የማይማረው” የሚለው ወሬ ቤተሰብ ጋር ደረሰ።” መማር ካልፈለገማ....” ተብሎ ብላቴናው ደረጀ ወደእረኝነት ሥራ እንዲሰማራ በቤተሰብ ተወሰነበት።

ለተወሰኑ ዓመታት ከነቡሬ ጋር ሜዳውን ሲያካልሉ የቆዩት ትንሹ ደረጀ የቀመሷት ፊደል ጣዕም ከውስጣቸው ስላልወጣች ወደትምህርት ቤት መመለስ ፈለጉ፡፡ በኋላም ፍላጎታቸው ተሳክቶ ተመልሰው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በንቃት በትጋት መከታተል ጀመሩ።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸው አመርቂ በሚባል ሁኔታ ያጠናቀቁት ጋሽ ደረጀ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃን በደነባ ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በደብረብርሃን ኃይለማርያም ማሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታተሉ። “የነብርን ጭራ አይዙም ከያዙም አይለቁም” በሚለው ብሂል ጋሽ ደረጀ በርትተው በመማር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ ካጠቃለሉ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ (ማትሪክ) ፈተና ወስደው ውጤት መጣላቸው፤ ይህንን ተከትሎም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን የመቀላቀል ዕድል አገኙ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ገብተውም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አገኙ። በመቀጠልም በአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ሥነ ዘዴ የሁለተኛ (ማስተማርስ) ዲግሪ አገኙ።

በትምህርት መስከ ያመጡት አጥጋቢ ውጤት ደግሞ ሌሎችን አስተምሮ ለመቅረጽ ዕድል ፈጠረላቸው። በዚህም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር አድርጎ እዛው አስቀራቸው። እነሆ እስከ ዛሬዋ እድሜያቸው ድረስም በዩኒቨርሲቲም የመምህርነት አበርክቷቸውን በአግባቡ እየተወጡ ይገኛሉ።

**በታላቁ ቤት የተገኘ ታላቅ ዕድል**

የአንጪቆረሩ ልጅ አድገው በአዲስ አበባው ዩኒቨርስቲ መምህር ከሆኑ በኋላ ከእረኝነት ቀጥሎ በተዋወቁት ሥራ በመምህርነት እድሜ ዘመናቸውን ቆተዋል። በዩኒቨርሲቲው በመምህርነት ከማገልገላቸውም በተጨማሪ፤ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አስተባባሪ በመሆን አገልግለዋል።

በዩኒቨርስቲው የሚዘጋጅ ዜና መጽሔት ላይ ማኔጂነግ ኤዲተር፤ የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር ነበሩ ።

ጋሽ ደረጀ ከማስተማሩ ጎን ለጎን የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን ያደርጋሉ። ከምርምሩም በላይ “ሀ” ተብላ በፊደል የተጀመረችውን የሥነ ጽሑፍ ክህሎት አሳድገው በርካታ መጽሐፍትን ለአንባቢያን ማበርከት የቻሉ መምህር ተመራማሪ ናቸው።

**ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎታቸው በጥቂቱ**

ጋሽ ደረጀ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን አስተማሪና አመራማሪ መጽሐፍትን እነሆ ብለዋል። ከእነዚህም ቀዳሚው ጠይም ዕንቁና ሌሎች የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ሲሆን ፤ መጽሐፉ የመጀመሪያ የምናብ ልጃቸው ሆኖ በ1981 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት ታትሞ ነበር ለንባብ የበቃው፡፡

ይህ መጽሐፍ መንደርደሪያም መነቃቂያም ሆኗቸው ከዛ በኋላ ባሉት ጊዜያት ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ፤ በተማሪዎች የቤት ሥራ የመምህራንና የወላጆች ሚና፤ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር፤ የዘመን ቀለማት የግጥም መድበል፤ ታትመውላቸዋል፡ ፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት የታተሙላቸው ሥራዎች አብዛኞቹ የልጆችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ እነሱም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በኩል የታተሙ ናቸው፤ ከእነሱም ውስጥ ጥቂቶቹ፣

ገበያ በገጠርና በከተማ፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤ 2010፤

መንገድና የመንገድ አጠቃቀም፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤

ግብርና፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤ 2010፤

ሥራና የሥራ እቅድ፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ

ባሕል፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤

ንጉሡና ገበሬው፣የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤

መጥፎ ተክል ሲነቀል፣ የንባብ መጽሐፍ ለ3ኛ ክፍል፤ 2010፤


ስፖርት፣ ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣

ግለታሪክ፣ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣

መገናኛ ብዙኀን፣ ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣ 2010፤

መዝናኛ፣ ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣ ፡፡

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**



ደረጀ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ፎቶ- ገበየ ገብሬ

> “ ጋሽ ደረጀ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን አስተማሪና አመራማሪ መጽሐፍትን እነሆ ብለዋል፡፡ ከእነዚህም ቀዳሚው ጠይም ዕንቁና ሌሎች የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ሲሆን ፤ መጽሐፉ የመጀመሪያ የምናብ ልጃቸው ሆኖ በ1981 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት ታትሞ ነበር ለንባብ የበቃው

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

ከገጽ 6 የዞረ



መጓጓዣ፣ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣ 2010፤

የአካባቢ ጥበቃ፣ ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍ ለ4ኛ ክፍል፣ 2010፤

ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ልጆችን በተረት ማስተማር (2011) አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡ ተረት እንደገና የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ማዳበሪያ አጋዥ፤ 2011፤ አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ድርጅት የሚሉ መጽሐፍት የመምህር ደረጃ የአዕምሮ ውጤቶች ናቸው ፡፡

በግል ጥረት ደግሞ፣ መራሔ ንባብ- የማንበብ ክሂል ማበልጸጊያ፤ 2013፤ አዲስ አበባ፤ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡ ጀግኖቻችን፣ አጫጭር የታዋቂ ግለሰቦች ታሪክ ለልጆች፤ 2013፤ አዲስ አበባ፤ ከቡክኮርነር ጋር በጋራ በመሆን ለተደራሲ አቅርበዋል።

**ከመጽሐፍቱ በተጨማሪ**

“በልጆች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ናሙናዊ የይዘት ትንተና፤ በአማርኝ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ምሳሌነት”፤ የሚል የጥናት ጽሑፍ፤ “በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ክረምት መርሐ-ግብር የክሬዲት ሰዓት ሥርዓት ትርጓሜና ተግባራዊነት ትንታኔ” የተዘጋጀ ጥናት “ኩርኩም ከጠፋ ልጅም አይፋፋ”፤ ታዛ መጽሔት፣ ደብረ-ያሬድ አሳታሚ ድርጅት፡፡ ግንቦት 2012፣ ቀጽ 3 ቁ. 32፣ ፅፈዋል።

“ለአማርኛ ማስተማር ሥነ ዘዴ (ቲም) መርሐ-ግብር ከ1985–96 የቀረቡ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (ዲማጾች) አጭር ቅኝት፤ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አሥራ ሰባተኛው ዓመታዊ ጉባኤ፤ ግንቦት 1997፣ (ገጽ 133– 150)

“በ1998 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት አዲስ የተመደቡ ተማሪዎች የመጀመሪያ ጽሑፍ ገጽታ”፤ ለ18ኛው የቋንቋዎች ጥናት ጉባኤ የቀረበ ጥናት (ከአቶ ግርማ ገብሬ ጋር በጋራ የተሠራ፣ በመድበለ ጉባኤ ለመታተም በሂደት ላይ ያለ)

“ስለ ባሕላዊ የዘፈን ግጥሞቻችን ጥቂት የመወያያ ሀሳቦች”፤ ታኅሣሥ 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በግሎባል ሆቴል ለሙዚቀኞች ማኅበር የቀረበና በብሌን ቁጥር 4 የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር መጽሔት፤

‹‹የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ዓላማዎች፣ ተግዳሮቶችና ጥቂት የመፍትሔ ሀሳቦች››፤ ብሌን፣ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር መጽሔት ቁ.7፣ ሰኔ 2003፣ ገጽ 10-13፡፡

በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ግምገማ” ለ19ኛው የቋንቋዎች ጥናት ጉባኤ የቀረበ፤ ሰኔ 1999 (ከአቶ ግርማ ገብሬ ጋር በጋራ የተሠራ፣ በመድበለ ጉባኤ በአ.አ.ዩ. ድረ ገጽ የታተመ)

“አጉል አስተያየቶች የሚያሸቃብጡ ዓይነት ከሆኑ ጭራሽኑ ሊገፈትሩ ይችላሉ”፤ ጠብታ መጽሔት፤ ቅጽ 1፣ ቁጥር 11 ( በመጽሐፍት የጀርባ ገጽ ላይ ስለሚሰጡ አስተያየቶች ቃለ መጠይቅ)፤

“ንባብ የእውቀት ምንጭ”፤ ስምዐ ጽድቅ፣ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፤ ጋዜጣ፡፡ 14ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18 ቅጽ 14 ቁጥር 137 እና 138፡፡

የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሦስት የአዲስ አበባ ት/ቤቶች የተደረገ ናሙናዊ ጥናት The Ethiopian Journal of Education. Vol. 27, Number 1 , June 2007 pp. 1 – 23.

‹‹የንባብ ልምድ ቅኝት በአዲስ አበባ›› Ethiopian Journal of Education (EJE), Vol. 29 No.2 December 2009 Pp. 69- 102.

‹‹አንጪቆረር ድፈሽ››፤ ታዛ መጽሔት፤ አዲስ አበባ፤ ደብረ-ያሬድ አሳታሚ ድርጅት፡፡ ቅጽ 2፣ ቁጥር 13፣ መስከረም-ጥቅምት 2011፤ ገጽ 31-33፡፡

**ማኅበራዊ አገልግሎት**

በበጎ አድራጎትና ከማኅበራዊ ግልጋሎት መስጠት የሚስደስታቸው እኚህ ሰው “ፕሮጃይኒስት” በተሰኘ ዋና ትኩረቱን በሴቶችና ሕፃናት ላይ ባደረገ ግብረ ሠናይ ድርጅት ውስጥ፣ በቦርድ አባልነት ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ነፃ ግልጋሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

በተጨማሪም “ልሕቀት የንባብ ማዕከል” በተሰኘ

**“….. ለሰው ሳደርግ መልሶ እንዲያደርግለኝ ሳይሆን እሱ ተሳክቶለት ሌላ የሱን እርዳታ የሚፈልግ ሰውን ለማገዝ እንዲችል በመመኘት ጭምር ነው**

ትኩረቱን በንባብ ባሕል መዳበር ላይ ባደረገ በጎ አድራጎት ድርጅትም ውስጥ የነፃ ግልጋሎት ሰጥተዋል። በኢትዮጵያ ራዲዮ፣ በፋና ራዲዮ፣ በሸገር ራዲዮ፣ በአሐዱ ራዲዮ ብዙ ጊዜ ከሙያዬና ከሥራ ልምዴ ጋር በተያያዙ ጥያቄዎችን በመመለስ ልምዴን አጋርቻለሁም ይላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በንባብ ልምድ፣ በልጆች ትምህርት፣ እና በመሳሰሉት ልምድና የሥራ የሥራ ተሞክሯቸውን በማቅረቡ በኩልም ሚናቸውን ይናገራሉ፡፡

በፋና ቴሌቪዥን በልዩ ልዩ ጉዳዮች (ማለትም ትምህርት፣ ድርሰት፣ የልጆች ንባብና ትምህርት፣ ስለመጽሐፎቼ ይዘትና አገልግሎት ወዘተ.) ላይ ለቀረቡልኝ ጥያቄዎች የማውቃቸውንና በደንብ የማምንባቸውን ሀሳቦቼን አጋራለሁ በማለትም ስለ ራሳቸው ያብራራሉ ፡፡

“......በተማሪዎች የቤት ሥራ የመምህራንና የወላጆች ሚና በተሰኘው መጽሐፌ ላይ የተንተራሱ በርካታ ገለጻዎችን በግል ትምህርት ቤቶች (በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባም ውጪ በአዋሳ፣ በመቂ፣ በሚዛን ቴፒ)፣ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰሜን ሸዋ አንጪቆረር አካባቢ ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ሁለት ጊዜ ልምድ አካፍያለሁ” ይላሉ፡፡

“......በሐምሌ 2016 ዓም በአሻም ቲቪ ላይ “መጽሐፈ ጨዋታ” በተሰኘ መርሐግብር ሙያዊ ገለጻ አድርጌያለሁ፡፡ ነሐሴ 2016 በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መዝናኛ ቻናል ስለ አንጋፋው ደራሲ ሣሕለሥላሴ ብርሃነማርያም በተሰናዳ የእውቅና ዝግጅት ላይ ሙያዊ ተሳትፎ አድርጌአለሁ”፡፡

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ በጀመረው “ብላቴናት” የልጆች መጽሔት ላይ ዓምደኛ በመሆን የረጅም ጊዜ የሥራ የጽሑፍ ልምዳቸውን እያጋሩም ይገኛሉ፡፡

**ሽልማቶቻቸው**

የተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ የተሳተፉት ጋሽ ደረጀ በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ሽልማቶች ከተለያዩ አካላት አግኝተዋል። ለምሳሌም በቅርቡ የተካሄደው የአስራ ሁለተኛው የበጎ ሰው ሽልማት የማኅበራዊ ጥናት ዘርፍ ተሸላሚ አድርጓቸዋል።

በሌላ በኩልም ለደራሲያን ማኅበር የዘመን ቀለማት በሚለው መጽሐፍ ላይ ስላደረጉት አስተዋፅዖ እውቅና የተሰጣቸው ሲሆን፤ በተጨማሪም በበጎ አድራጎት ሥራቸው ከተሳተፉባቸው አብዛኛው የእውቅና ሰርተፍኬት አግኝተዋል።

በሕይወት መንገድ

ጋሽ ደረጀ በሕይወቴ አላሳካሁትም ይቆጨኛል የሚሉት ነገር እንደሌላቸው ይናገራሉ። በትዳር ሕይወታቸው ደስተኛ በሥራቸውም ስኬታማ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ለሌሎች ማካፈል እጅግ በጣም የሚያስደስታቸው ተግባር መሆኑን ይናገራሉ።

ሰው ይታይልኝ እየተባለ ለሰው በሚያደርግበት ዘመነ ለተቸገረው ደራሽ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፤ ያለውን ተካፍሎ የሰውን ሕይወት ማቅለል ተገቢ ነው ብለወም ያምናሉ ።

“..... ለሰው ሳደርግ መልሶ እንዲያደርግለኝ ሳይሆን እሱ ተሳክቶለት ሌላ የሱን እርዳታ የሚፈልግ ሰውን ለማገዝ እንዲችል በመመኘት ጭምር ነው። በዩኒቨርሲቲ ግቢ ለሚኖሩ ለሻይ የሚሆን ሳንቲም ለሚቸገሩ ልጆች የምችለውን ከማድረግ ጀምሮ እስከመመረቂያ ሙሉ ልብስ ድረስ እገዛለሁ። ከዚህም በተጨማሪ በሰሜን ሸዋ አካባቢ ተማሪዎችን የሚያግዝ ድርጅት ውስጥም አገለግላለሁ” በማለት መስጠት ማካፈል የሚሰጣቸውን ደስታ ይናገራሉ።

የተማረ ያስተምር ነፃ የትምህርት አገልግሎት (ስኮላር ሽፕ) ፈንድ የተሰኘ የተቸገሩ ተማሪዎችን የሚረዳ በተለይም ሴት ተማሪዎች ተበረታተው ውጤታማ የሚሆኑበትን ድጋፍ ያደርጋል። ጋሽ ደረጀም በዚህ አሜሪካን ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተቋቋመ በጎ አድራጎት ኮሚቴ ውስጥ ከአስተባበሪዎቹ አንዱ በመሆን አገልግለዋል።

በመጨረሻም

“......ከላይ እንዳልኩት እኔ በሕይወቴ ቀረ የምለው ወይንም ባደርገው ኖሮ ብዬ የምቆጭበት ነገር የለኝም። ባገኘሁት ዕድል ብዙ ወጣቶችን አስተምሬ አብቅቻለሁ። አሁንም እያስተማርኩ ነው። ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል” ካሉ በኋላ ወጣቶች ተምሮ መለወጥን ባላቸው አውቀትና ችሎታ ለሌሎች መትረፍን ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ነገር ስለመሆኑም አጥብቄ እናገራለሁ። በጎነት የአንድ መልካም አሳቢ ሰው የብቻ ባሕሪው አይመስለኝም፤ የሌሎችንም በርካታ ተባባሪዎች የሚፈልግ ተግባር ነው፤ በጎነት እንዲቀጥል በጎዎች ይብዙልን፡፡” በማለት ከሰፊው የማስተማርና የሕይወት ልምዳቸው ያገኙትን ዕውቀት በጥቂቱ አካፍለውናል፡፡

# የቱሪስት ቆይታን ለማራዘም- የአስጎብኚ ባለሙያዎች ሚና

**ዳግም ከበደ**



**የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር ከሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች አንዱ ነው**

ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ከሚታመንባቸው መካከል የአስጎብኚ ባለሙያዎች ይጠቀሳሉ። ባለሙያዎቹ በቀጥታ ከቱሪስቱ ጋር የሚሠሩና በቆይታው ወቅት አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉ እንደመሆናቸው በበጎም ሆነ በአሉታዊ መንገድ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ከፍ ያለ ነው።

በተለይ ቱሪስቶች በመስሕብና በመዳረሻ ቦታዎች ላይ ለሚኖራቸው የተራዘመ ቆይታ የአስጎብኚዎች ምክረ ሀሳብ እና ሙያዊ ብቃት ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። በመሆኑም ዘርፉን በመዳረሻ ልማት፣ በገበያና ማስተዋወቅ ከማደራጀት ባሻገር ብቁና ሙያዊ ሥነምግባር ያለው አስጎብኚም በብዛት ማፍራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ የበርካታ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባሕላዊና ሌሎች የቱሪዝም መስሕቦች መገኛ ነች። በተለይ በያዝነው የመስከረም ወር የሚከበሩ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶች የቱሪስትን ቀልብ የሚስቡ፣ ሀገሪቱን በበጎ ገፅታ ከማስተዋወቅ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያረጋግጡ ናቸው። ባሳለፍነው ሐሙስና ዓርብ የተከበረውና በዩኔስኮ የዓለም አቀፍ የማይዳሰስ የሰው ልጅ ወካይ ቅርስ ተብሎ እውቅና የተሰጠው የመስቀል ደመራ በዓል የዚሁ የሀገሪቱ ሀብት ውጤት ነው። በቀጣይ ሳምንት ቅዳሜና እሁድ በአዲስ አበባና በቢሸፍቱ የሚከበረው የኢሬቻ በዓልም እንዲሁ የዚሁ አካል ነው።

እነዚህን ሀብቶች ለመመልከት በርካታ ቱሪስቶች ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች እና ከሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች ይመጣሉ። በተለይ የውጪ አገር ጎብኚዎች የቱር ኦፕሬተሮችንና የጎብኚዎችን ምክረ ሀሳብ ተከተለው፤ ታሪክ፣ ባሕልና ሃይማኖት ነክ የሆኑ መስሕቦች ላይ ይታደማሉ፤ ጉብኝት ያደርጋሉ። በዚህ ወቅት አስጎብኚ ባለሙያዎች አንድ ቱሪስት በአግባቡ መስተንግዶ አግኝቶ፣ የኢትዮጵያን እሴቶች ተዋውቆ ወደ አገሩ እንዲመለስ ሙያዊ ድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል። በተለይ ጎብኚው ቆይታው እንዲያራዝምና ሌሎች መስሕቦችንም እንዲመለከት ለማድረግ አስጎብኚው በሚገባ መሥራት ይጠበቅበታል።

አቶ ክብሮም ተስፋይ የኢትዮጵያ አስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት ናቸው። ኢትዮጵያ አዲስ ዓመት (2017 ዓ.ም.) ከመግባቱ ከነሐሴ ወር ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ በዓላት እንደሚከበሩ ይናገራሉ። በተለይ በመስከረም ወር የማኅበረሰቡን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶች አጉልተው የሚያሳዩ ክብረ በዓላት የሚዘጋጁበት ወቅት መሆኑን ይገልፃሉ።

ከእነዚህ መስሕቦች ውስጥ በቱሪዝም ዘርፍ ያስተዋወቅናቸውና ለዓለም አቀፍ ጎብኚዎች እንዲታዩ ያደረገናቸው የተወሰኑትን ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከሻደይ አሸንዳ የልጅ አገረዶች በዓል ጀምሮ፣ በደቡብ ክልል የሚከበሩትን የአዲስ ዓመት መግቢያ በዓላትን (የጌዲዮ፣ የሀድያ፣ የየም እና ሌሎችንም) ጨምሮ በርካታ ሀብቶች መኖራቸውንም ይገልፃሉ።

መስሕቦቹን በሰፊው ማስተዋወቅ ቢቻል በኢኮኖሚውም ከፍተኛ ጥቅም የሚፈጥሩ እንደሆኑም ይናገራሉ። ሰፊና የየራሳቸው ዓውድ ያላቸው ክብረ በዓላት ከመሆናቸው አንፃር በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀላል ወጪ ሁሉንም ማስተዋወቅ እንደማይቻል የሚናገሩት ባለሙያው፣ ይህን መሰል አቅም ለመፍጠር ከፍተኛ በጀት፣ ብቁና የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት እንደሚገባም ይገልፃሉ።

‹‹በመስከረም ወቅት ያሉትን ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶችን ወደ ቱሪዝም መስሕብነት ቀይሮ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል›› የሚሉት አቶ ክብሮም፤ ኢትዮጵያ ያላት የመስሕቦች ብዛት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ቢሆንም ቱሪዝም ዘርፉ ይህንን ወደ አቅም ለመቀየር የሚያስችል ትክክሻ መፍጠር አለበት ይላሉ። በዚህ ረገድ የአስጎብኚ ባለሙያዎች ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ በመሠረተ ልማት፣ በትራንስፖርት፣ በአገልግሎት ዘርፍ፣ በሠለጠነ የሰው ኃይል፣ አሠራርን ከማዘመን አንፃር ከመንግሥት ተቋማት ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የቱሪስት አስጎብኚዎች ማኅበር ከነሐሴ ወር ጀምሮ በመስከረም ወር የሚከበሩ የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲተዋወቁና ጎብኚዎች መዳረሻ እንዲያደርጓቸው እየሠራ መሆኑን የሚያነሱት አቶ ክብሮም፤ የመጀመሪያው የባለሙያዎቹ ሥራ ሀብቶቹን የመለየትና በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እንዲሁም በምን መልኩ እንደሚከበሩ መገንዘብ መሆኑን ይገልፃሉ። ከዚህ አኳያ በዚህም የማኅበሩ አባላትና አስጎብኚዎች እነዚህን እሴቶች ለይተው እንዲያውቁ ሥልጠናና በግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ አስጎብኚ ባለሙያዎች እንደ መስቀል፣ ኢሬቻ እንዲሁም ሌሎች ክብረ በዓሎች ላይ ከደኅንነት አንፃር ሊወሰድ ስለሚገባ ጥንቃቄ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን ግንዛቤ ለማስጨበጥም የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚዎች ማኅበር አባላት ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። የመስቀል በዓል በተከበረበት ወቅትም ከሥልጠናው የተገኙ ልምዶች በአስጎብኚ ባለሙያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዓላቶች ላይ ለመታደምና በኢትዮጵያ የሚገኙ መስሕቦችን ለመጎብኘት የሚመጡ ቱሪስረቶች ደኅንነት መጠበቅ የአስጎብኚውም ኃላፊነት እንደሆነ የማስገንዘብ ሥራ ተሠርቷል። በጉብኝት ሰበብ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ አደናጋሪዎችን ከትክክለኛ ጎብኚዎች መለየትና ጥንቃቄ መውሰድም እንዲሁም የአስጎብኚው ደርሻ አንደሆነ የማስረዳት ሥራዎች በተከታታይ በማኅበሩ በኩል ተከናውነዋል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ በአዲሱ ዓመት መስከረም ወር በኢትዮጵያ በርካታ የቱሪዝም ሁነቶች ይካሄዳሉ። በመሆኑም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ጎብኚዎች በአንድ ቦታና ሁነት ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እሴቶች እውቀትና ልምድን ይዘው እንዲመለሱ የማድረግ ኃላፊነት የአስጎብኚ ባለሙያዎች ነው። በመሆኑም ማኅበረሰቡ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና የተለያዩ የማኅበረሰብ እሴቶችን ለጎብኚዎች ከማሳየት፣ በአንድ አካባቢ ላይ ብቻ የቱሪስት መጨናነቅ እንዳይኖር ከማድረግ አንፃር ልዩ ልዩ ስልቶች ተቀርፀው ተግባራዊ ተደርገዋል።

በመስከረም ወቅት በአደባባይ በዓላት ላይ ለመታደም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ጎብኚዎች ስለ ክብረ በዓሎቹ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ሲሄዱ በበጎ መልኩ እንዲያስተዋውቁ አስጎብኚዎች ድርሻቸውን እየተወጡ ነው። ስለ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓሎቹ ምንነትና ትርጓሜም ትክክለኛው መረጃ እንዲኖራቸው በበዓሉ ወቅትም ሆኖ ከዚያ ቀደም ብሎ የማስገንዘብ ሥራ እየተሠራ ነው። ይህንን ኃላፊነት የማኅበሩ አባላት እንዲወስዱ ተደርጓል።

‹‹የአደባባይ በዓሎቹ የቱሪስቱን ቆይታ ሊያራዝም በሚችል አግባብ በትክክል ሊተዋወቁ ይገባል›› የሚሉት አቶ ክብሮም፤ በተጨማሪ ከፍተኛ ቱሪስት በሚገኝበት በዚህ ወቅት ከዚህ ቀደም ምንም ያልተዋወቁ አዳዲስ መስሕቦችን አጋጣሚውን ተጠቅሞ ለጎብኚዎቹ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ። ለምሳሌ ያህል የሸዋል ኢድ በዓል፣ የድሬ ሼክ ሁሴን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚከበሩ የአዲስ ዓመት በዓላትና ሌሎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስሕቦችን ማስተዋወቅ ይገባል። ይህንን ለማድረግ የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር አቅጣጫ በማስቀመጥ ተግባራዊ ሥራዎችን እያከናወነ ነው ብለዋል።

የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት እንደሚገልፁት፤ ቱሪስቶች በብዛት ከሚገኙባቸው ከተለመዱት የቱሪስት መዳረሻ መስሕቦች በተጨማሪ አዳዲስ ያልተዋወቁ ሀብቶች ላይ መሥራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል በገና ወቅት ላሊበላ ልዩ ትኩረት አግኝቶ ቱሪስቶች ለጉብኝት ይሄዳሉ። ይሁን እንጂ የጊዮርጊስ በዓል በሚከበርበት ወቅት ለቱሪስቶች ልዩ ድምቀትና ልምድን የሚሰጥ ክብረ በዓል አለ። በትግራይ አክሱም ጽዮንም ከኅዳር ዓመታዊ ክብረ በዓል ባሻገር የዓብይ ፆም ሊፈታ ሲቃረብ በሆሳዕና በዓል የቱሪስቶችን ቀልብ ሊስብ የሚችል ክብረ በዓል አለ። ይህንን አይነቱን አዳዲስ ልምድ በማስተዋወቅ ጎብኚዎች ተጨማሪ አማራጭ እንዲያገኙና ኢትዮጵያን እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚዎች ማኅበርም አዳዲስ መስሕቦችና መዳረሻዎች የሚከበሩበትን ወቅት፣ ስፍራ እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች የሚሰጥ ካላንደር ለማዘጋጀት እየሠራ ነው። ይህንን ካላንደር ከባለሙያዎች፣ ከባሕልና ሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም ከመንግሥት ባለድርሻ ጋር ማዘጋጀት ቢቻል በያዝነው መስከረም ወር ከሚከበሩት ደማቅ ክብረ በዓሎች ባሻገር አዲስ መዳረሻን በመፍጠር የቱሪስት ቁጥር ሽፋን ማሳደግ ይቻላል።

የቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ በዩኔስኮ እውቅና ያላቸውም ሆነ ገና በሂደት ላይ የሚገኙ መስሕቦችን ከማስጎብኘት ባሻገር ተጨማሪ የቱሪስቱን ቆይታና ተዝናኖት የሚጨምሩ ሁነቶችን ለመፍጠር እየሠራ መሆኑንም አቶ ክብሮም አስታውቀዋል፤ ከዚህ ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ያዘጋጀው አስጎብኚዎች በመስሕብ ስፍራዎቹ ሲንቀሳቀሱ በምስል (ፎቶ) ያስቀሯቸውን ማራኪ የጉብኝት ቦታዎች የሚያሳይ ዓውደ ርዕይ መሆኑን ይናገራሉ። ዘንድሮም የመስቀል፣ ኢሬቻና በደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚያከብሯቸው በዓላትን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ሙዚየም ዓውደ ርዕይ መካሄዱን ይናገራሉ።

‹‹የፎቶ ዓውደ ርዕይው ሁለት ዓላማ ነው ያለው ነው›› የሚሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ የመጀመሪያው አጠቃላይ ማኅበረሰቡ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ስለሚገኙ የመስሕብ ሀብቶች (ስለሰሜኑ ደቡቡ፤ ምስራቁ ስለ ምዕራቡ) ግንዛቤ ኖሮት የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲያድግ ማድረግ መሆኑን ያነሳሉ። ሁለተኛው በኢትዮጵያ ኤምባሲ የከፈቱ ሀገራት አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶችን በመጋበዝ በቀላል ወጪና በአጭር ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ለየሀገሮቻቸው ዜጎች እንዲያስተዋውቁ ዕድል መክፈት መሆኑን ገልጸዋል።

የማኅበሩ የአስጎብኚ ባለሙያዎች አባላት እንደ ሌሎች የፎቶ ዓውደ ርዕዮች የመስኅብ ሰፍራዎችን ብቻ በፎቶ በማስቀመጥ የሚያስተዋውቅበት መድረክ አይደለም ያሉት አቶ ክብሮም፤ ይልቁኑም አንድ ጎብኚ ወደ መዳረሻዎቹ ቢያቀና በቀላል ወጪ የሚያርፍበትን ሆቴል፣ ማግኘት ስለሚችለው ልዩ ልዩ አገልግሎት፣ ሊጎበኛቸው የሚችላቸው መዳረሻዎች ብዛት እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ ማስረጃዎችን ጭምር በዓውደ ርዕይው ማግኘት እንደሚቻል ያስረዳሉ። ለሦስተኛ ጊዜ የተዘጋጀው ዓውደ ርዕይም ይህንን ዓላማ ያሳካ እንደነበር ተናግረዋል።

‹‹መስከረም በኢትዮጵያ የቱሪዝም ወር እየሆነ ነው›› የሚሉት የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተለይ ለኢትዮጵያውያን የአዲስ ዓመት መጀመሪያ፣ የክረምት ወር መውጫ፣ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የአደባባይ በዓላትና የዓለም የቱሪዝም ቀን የሚከበሩበት መሆኑን ይገልፃሉ። በዚህ ምክንያት የፎቶ ዓውደ ርዕይ በዚህ ወር ቢዘጋጅ ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ ሰፊ ቁጥር ያለው ጎብኚ ማግኘት እንደሚቻል በማመን በዚህ ወር መደረጉን ገልጸዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንቱ መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር ተባብሮ የኢትዮጵያን የመስሐብ ሀብቶች ለማስተዋወቅ፤ ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ መሥራት እንደሚጠበቅበትም አመልክተዋል። የአደባባይ በዓል የሆኑት መስቀል፣ ኢሬቻና ሌሎችም በዓላት አሁን ካሉበትም በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲተዋወቁ ሰፊ ጥረት መደረግ ይኖርበታል ይላሉ።

ቱሪዝም ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ተደርጎ ከመወሰዱ አንፃር ይህንን እድል ማስፋት የሚያስችል የቱሪዝም ሚኒስቴር መዋቅር ሊዘረጋ ይገባል ሲሉም ጠቁመዋል። አሁን ያለው አደረጃጀት ኢትዮጵያ ካላት አቅም፣ ለዘርፉ ከተሰጠው ልዩ ትኩረት አንፃር ሲመዘን በቂ ነው ተብሎ እንደማይታመንም ያነሳሉ። በመሆኑም ጠንካራ የቱሪዝም ሚኒስቴር እና ሌሎች መንግሥታዊ አደረጃጀቶችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

በሌላ በኩል ቱሪዝም ሠላም እንደሚፈልግ ተናግረው፤ ሠላም ለቱሪዝም ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን አፅንዕኖት ሰጥተው አመልክተዋል። ማኅበረሰቡ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ በዓላት በሚከበሩበትም ሆነ በየትኛውም ጊዜ የራሱን ሠላም እና ደኅንነት በማስጠበቅ የአገሪቱን መልካም ገፅታ ሊገነባና የቱሪስቶችን ደህንንት እንዲጠብቅም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የአዲስ ዓመት ባለ ታሪኮች

**ዋስልኝ አየለ**

ዓመተ ምሕረት ከቀየርን እነሆ ዛሬ 19ኛ ቀናችን ነው። መስከረም ዘመን የሚቀየርበት ወር ስለሆነ ሙሉውን ‹‹አዲስ ዓመት›› ተብሎ ይጠራል። በታሪክ ውስጥ ደግሞ ዓመተ ምሕረት ትልቅ ቦታ አለው። በምንጠቅሳቸው ታሪኮች ውስጥ ‹‹ከ...ዓመታት በፊት›› የምንለው ቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው። በሌላ በኩል አዳዲስ ተጨማሪ ታሪኮች ይኖራሉ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ከሦስት ዓመት በፊት በዚህ ሳምንት የሙዚቃው ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠ ይታሰብ ነበር። እነሆ ከ2015 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ተጨመረ ማለት ነው። አንደኛው በውልደት አንደኛው በሞት የዚህ ሳምንት ክስተቶች ይሆናሉ ማለት ነው። ‹‹ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም›› የሚባለው ለታሪክ ክስተቶች ነው።

ከዘመናት በፊት የተከሰቱ የዚህ ሳምንት የታሪክ ክስተቶችን ስናስታውስ ቅይጥ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለዛሬው አንዱን ብቻ መርጠን በዝርዝር ከማየት ይልቅ የሁሉንም አጠር አጠር አድርገን ማየት መረጥን። በቀናቸው ቅደም ተከተል መሠረት እንያቸው።

ከ78 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 15 ቀን 1939 ዓ.ም የመጀመሪያው የአማርኛ ረጅም ልብወለድ መጽሐፍ (‹‹ጦቢያ››) ደራሲ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ዘብሄረ ዘጌ አረፉ። አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በሀገርኛ ቋንቋ በመጻፍ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ የተባሉ ናቸው። በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ‹‹የኢጣሊያ መንግሥት መልዕክተኛ ሆነው አገልግለዋል›› ተብለው የዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው፣ የእቴጌ ጣይቱ ዘመድ (ግን ደግሞ እቴጌዋ በአንድ የስዕል ሥራ ምክንያት የጠሏቸው) ናቸው። አፈወርቅ ገብረኢየሱስ የኢጣሊያ መንግሥት መልዕክተኛ ሆነው በማገልገላቸው ከመታሰራቸውም ባሻገር በታሪካቸው ‹‹ባንዳ›› የሚል ወቀሳ አትርፈዋል።

‹‹ጦቢያ›› በሚለው መጽሐፋቸው የመጀመሪያው ረጅም ልቦለድ ጸሐፊ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። መጽሐፉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ‹‹አጤ ምኒልክ›› የሚለውን በመጨመር ሁለት መጽሐፍ አንድ ሆኖ (በማዟዟር) በገበያ ላይ ይገኛል። በብዙ የሥነ ጽሑፍ መድረኮችና ውይይቶችም ‹‹ጦቢያ›› የሥነ ጽሑፍ መነሻ ተደርጋ ትጠቀሳለች።

አሁን ደግሞ 358 ዓመታትን ወደኋላ እንሂድ። በዚሁ ሳምንት መስከረም 15 ቀን 1659 ዓ.ም ከጎንደር ነገሥታት አንዱ የነበሩት አፄ ፋሲል አረፉ። የአጼ ፋሲል ታሪክ ከጎንደር ነገሥታት ሁሉ ጎላ ብሎ ይታወቃል። አጼ ፋሲል ከ18 የጐንደር ነገሥታት አንዱ ሲሆኑ የአጼ ሱስንዮስ ልጅ እና የአጼ ዮሐንስ አዕላፍ ሰገድ አባት ናቸው። አጼ ፋሲል በታሪክ ውስጥ ዛሬ ድረስ ሕያው እንዲሆኑ ካደረጓቸው ነገሮች አንዱ የዓለም ቅርስ የሆነው የፋሲል ግንብ ነው። አጼ ፋሲል ፋሲለደስ እየተባሉም ይጠራሉ። በዚህም ምክንያት በስማቸው ትምህርት ቤቶችና እና ክፍለ ከተሞች ተሰይመዋል።

ከ95 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በደመራ ዕለት መስከረም 16 ቀን 1922 ዓ.ም ‹‹ሞገደኛው›› ደራሲና ጋዜጠኛ መንግሥቱ ገዳሙ ተወለደ። መንግሥቱ ገዳሙ በርካታ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አሉት። መንግሥቱ ‹‹ሞገደኛው›› የሚለው ሥያሜ የተሰጠው ከልጅነቱ ጀምሮ ችኩል፣ ቁጡና ስህተቶችን የማይታገስ ስለነበር ነው ይባላል። በዚህም ምክንያት ሞገደኛ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶት ያ ስም አብሮት ዘለቀ። ካደገ በኋላም የሰውየው ባሕሪ ወጣ ያለ የሚባል ነበር። በሕይወት እያለ ‹‹መንግሥቱ ገዳሙ ሞቷል›› ብሎ በራሱ ላይ መርዶ ያስነገረ ደፋር ነው። በተደጋጋሚ ሚስት እያገባ በመፍታት ‹‹የሴቶችን ባሕሪ ለማወቅ ነው›› በማለት በራሱ ሕይወት ላይ ጥናት ያደርግ ነበር። የሚሠራበት መሥሪያ ቤት ውስጥ በርኖስ ለብሶ በመግባት ‹‹ኧረ ባክህ የሥራ አለባበስ ሥነ ሥርዓት አይደለም›› ሲሉት ‹‹ባሕሌን ለማስተዋወቅ ነው›› በማለት ይሟገት ነበር። በአጠቃላይ በእነዚህ ባሕሪያቱ ‹‹ሞገደኛው›› የሚል ቅጽል ስም አትርፏል።

ከ108 ዓመታት በፊት የመስቀል ዕለት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን ተሽረው፣ ዘውዲቱ ምኒልክ ‹‹ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ›› ተብለው በአባታቸው፣ በዳግማዊ ምኒልክ፣ ዙፋን ተቀመጡ። ደጃዝማች ተፈሪ መኮንንም ‹‹ራስ ተፈሪ›› ተብለው አልጋ ወራሽ ሆኑ። ሙሉ ዝርዝሩን በጥቅምት ወር የሰገሌ ጦርነትን በምናስታውስበት ታሪክ እናስነብባችኋለን።

ከ84 ዓመታት በፊት ልክ የመስቀል ዕለት መስከረም 17 ቀን 1933 ዓ.ም ዝነኛው ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ ተወለደ። ታሪክህ ከበዓል አይራቅ የተባለው ጥላሁን ገሠሠ የመስቀል ዕለት ተወልዶ ከ68 ዓመታት በኋላ በፋሲካ በዓል ዕለት አረፈ። ፋሲካ የሚውልበት ቀን ስለሚለያይ በየዓመቱ የፋሲካ ዕለት ላይታወስ ይችላል። ሆኖም ግን ያረፈበት ሚያዚያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ይታወሳል። ጥላሁን ገሠሠ በየዓመቱ በብዙ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሲታወስ አስተውያለሁ።

መስከረም 17 ቀን በዓመቱ ጥላሁን ገሠሠን እያስታውስን ሳለ፤ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅም የዚሁ ታሪክ አካል ሆነ። አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በድንገት ሕይወቱ ያለፈው ከሁለት ዓመት በፊት መስከረም 17 ቀን 2015 ዓ.ም ነበር።

ከ64 ዓመታት በፊት መስከረም 17 ቀን 1953 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት በልዩ ልዩ መንገዶች ለኢትዮጵያ አጋርነታቸውን ያሳዩት እንግሊዛዊቷ የኢትዮጵያ ጠበቃና ባለውለታ ወይዘሮ ሲልቪያ ፓንክረስት አረፉ። ሲልቪያ ፓንክረስት የታዋቂው የታሪክ ምሑርና ልክ እንደርሳቸው ሁሉ የኢትዮጵያ ባለውለታ የነበሩት የፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት እናት ናቸው።

ከ160 ዓመታት በፊት መስከረም 19 ቀን 1857 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቁንጅና ውድድር ተካሄደ። ብዙም ሲነገርለት ስለማይሰማ፤ የጳውሎስ ኞኞን አጤ ቴዎድሮስ መጽሐፍ ዋቢ በማድረግ ዘርዘር አድርገን እንየው።

የመስቀል በዓል በዋለ በሁለተኛው ቀን፣ ከልደታ ምሥራቅ ለአበራ ጊዮርጊስ ሰሜን ከሆነችው በቀሃ ወንዝ አጠገብ፣ አጤ ሰቀላ ላይ ከምትገኘው ኮረብታ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ሸራ ድንኳን ተተከለ። ከጧቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ የከተማውና የገጠሩ ሕዝብ በዓሉ ወደሚከበርበት ሜዳ ይጎርፍ ጀመር።

ከረፋዱ አራት ሰዓት ሲሆን ምርጥ መሣሪያ የያዙ ወታደሮችና አጋፋሪዎች ሰልፈኛውን ለማስተናበርና ፀጥታውን ለማስከበር በበዓሉ ሜዳ ተሰማሩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬ በሠራዊታቸው ታጅበው ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ አጤ ሰቀላ ደረሱና የዙፋኑን አቀማመጥ ተመለከቱ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በፈረሶች በሚሳብ ሰረገላ ላይ ተቀምጠው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል ባሠለጠናቸው ወታደሮች ታጅበው መጥተው በዙፋናቸው ላይ እንደተቀመጡ እምቢልታና መለከቱ ተብላላ፤ አጅብር አጅብር፣ ውጋው ውጋው እያለ ነጋሪት ይጎሰም ጀመር።

ዘፋኞች ይዘፍናሉ፤ አዝማሪዎች ይዘምራሉ፤ ወታደሮች ይጨፍራሉ። በዚህ ዓይነት ይዞታ ተድላና ደስታ ሆኖ ሲደባለቅ በመካከሉ ለውድድሩ የታጩት ወይዛዝርት ጥልፍ ቀሚሳቸውን እያንሰረተቱ፣ ተቀብተውና ተኳኩለው ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ያልፋሉ።

ቀጥሎም ምርጫው በሚፈፀምበት ጎል እየገቡ ውበታቸውና ደም ግባታቸው፣ የላሕየ ገፃቸው አወራረድ፣ የፀጉራቸው ስሬት፣ የቁንዳላቸው ርዝመት፣ ሽንጣቸው፣ ዳሌያቸውና ተረከዛቸው እየተመረመረ የምርጫው ሥነ ሥርዓት ይጀመራል። እንዲህ እየተደረገም ከሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም የመጣችው ትውልዷ ከመቄት አዝማቾች ወገን የሆነችው የደጃዝማች ይልማ አሰፋ ልጅ፣ ጣይቱ ይልማ አንደኛ ስትሆን፣ ከጎንደር አዲስ ዓለም የመጣችው የመሐመድ ኩርማን ሚስት የሼህ መሐመድ ጌታ ልጅ፣ ተዋበች መሐመድ ደግሞ በፀጉሯ ማማር፣ በቁንዳላዋ አወራረድና መርዘም ሁለተኛ ደረጃን አገኘች።

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል የምርጫውን ውጤት ለንጉሠ ነገሥቱ ለመንገር ወደ ዙፋኑ ቀረቡ። ወዲያውም ጣይቱ ይልማ አንደኛ፣ እንዲሁም ተዋበች መሐመድ ጌታ ሁለተኛ መሆናቸውን ከገለፁ በኋላ ተመራጮቹ ከዙፋኑ ፊት በመቅረብ እጅ እየነሱ ሽልማታቸውን ተቀብለው የበዓሉ ፍፃሜ ሆነና እንደተለመደው በሰባት ሰዓት ለመሳፍንት፣ ለሊቃውንት ለመኳንንትና ለካህናት የምሳ ግብዣ ተደረገ።

ከውድድሩ በኋላ አርማኤል (ወርመር) የተባለው በጋፋት የመድፍ ሠራተኞች አለቃ አንደኛ የወጣችውን ጣይቱ ይልማን በሚስትነት አግብቶ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወልደዋል። ጋይንት ውስጥ አሁንም በአርማኤል ስም የሚጠራ መሬት አለ።

**በዚሁ ሳምንት መስከረም 15 ቀን 1659 ዓ.ም ከጎንደር ነገሥታት አንዱ የነበሩት አፄ ፋሲል አረፉ:: የአጼ ፋሲል ታሪክ ከጎንደር ነገሥታት ሁሉ ጎላ ብሎ ይታወቃል:: አጼ ፋሲል ከ18 የጐንደር ነገሥታት አንዱ ሲሆኑ የአጼ ሱስንዮስ ልጅ እና የአጼ ዮሐንስ አዕላፍ ሰገድ አባት ናቸው**

በምዕራቡ ዓለም ደግሞ ዘመናዊ የቁንጅና ውድድር መካሄድ የጀመረው በ1831 ዓ.ም በስኮትላንድ እንደሆነ የታሪክ ማስረጃዎች ያሳያሉ። በወቅቱ ተደርጎ በነበረው ውድድር ያሸነፈችው ከገዢ መደብ አባላት የሆነች ሴት እንደነበረች ተፅፏል።

በ1847 ዓ.ም በአሜሪካ የቁንጅና ውድድር ለማድረግ ተሞክሮ ብዙ ሳይጓዝ መቋረጡም ይነገራል። የቁንጅና ውድድር በመላው ዓለም በስፋት እየታወቀ የመጣው ግን በ1881 ዓ.ም በቤልጂየም ከተካሄደው የቁንጅና ውድድር ወዲህ እንደሆነ ማስረጃዎቹ ያመለክታሉ። ለማንኛውም ኢትዮጵያ የቁንጅና ውድድርን የጀመረችው ከ159 ዓመታት በፊት ነው።

ከ89 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወረረች። ይህም የአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ቆይታ መጀመሪያ ሆነ ማለት ነው።

ከ108 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 24 ቀን 1909 ዓ.ም ንጉሥ ሚካኤል ዓሊ በልጃቸው፣ ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን መወገድ ምክንያት ተበሳጭተው ጦራቸውን አስከትተው ወደ ሸዋ እየገሰገሱ እንደሆነ የሰሙት የማዕከላዊው መንግሥት ሹማምንት (የሸዋ መኳንንት) ለንጉሥ ሚካኤል ደብዳቤ ጻፉላቸው። ደብዳቤውም ይህ ነበር።

‹‹...ይድረስ ከንጉሥ ሚካኤል። ዘሥልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ንጉሠ ጽዮን።

ልጅዎ ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ የልጅ ሥራ እንደሆነ ንጉሡም ያውቁታል። እኛም መክረን ተቆጥተን እናሳድጋለን ብለን ብናስብ ባንድ ስፍራ የማይቀመጡ ስለሆነብን ጊዜ አላገኘንም። አንዳንድ ጊዜም እያገኘን ብንመክራቸው አልተቀበሉንም። እኛም ምናልባት ከነገ ሣልስት የመንግሥታቸውን ጥቅም፤ የራሳቸውን ማዕረግና ክብር እያወቁ ይህን የልጅነት ሥራቸውን ይተውት ይሆናል በማለት ሰውነታቸው እንዳይሳቀቅ ታግሰን ብንጠብቃቸው የልጅነት ሥራ መሥራታቸው አልበቃ አላቸው። ... ይህንንም ሁሉ ታግሰን ሁላችንም ባንድነት ሆነን ሊቀ ጳጳሱንና እጨጌውን ጨምረን ለማናቸውም ቢሆን ለእንቁጣጣሽ (ላዲሱ ዓመት) ወደ አዲስ አበባ ይምጡ ብለን ደብዳቤ ጽፈን ብንልክላቸውም ሳይመጡ ቀሩ። ይህንም ሁሉ ለንጉሥ መጻፋችን አጼ ምኒልክን እኛንም ሁሉ እንዲወዱ እናውቃለንና አሳብዎ ከአሳባችን ሳይለይ በአንድነት እንድንቆም እንጂ በተለየ ንጉሥ እንዲቀየሙና ልጅ ኢያሱ እንዲጎዱ ብለን ያደረግነው አይደለም። መስከረም 24 ቀን 1909 ዓ.ም...››

ከ8 ዓመታት በፊት መስከረም 25 ቀን 2009 ዓ.ም ወደር በሌለው የጦር ሜዳ ጀግንነታቸው የሚታወሱት ብርጋዴር ጀኔራል ለገሠ ተፈራ ወልደሥላሴ አረፉ።

አምስት የሶማሊያ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮችን ያጋዩት፣ የሶማሊያን ተዋጊ ጄቶች እርስ በእርሳቸው አላትመው ያነደዱት፣ ጀት አብራሪው እና የበረራ አስተማሪው፣ የሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቁ፣ ሳይሰለቹ የመብረር፣ በአየር ላይ የመገለባበጥ፣ ዒላማ የማስገባትና ምንም ጭስ ሳያሳዩ የማረፍ ልዩ ተሰጥዖዎች ባለቤቱ፣ የፕሬዚዳንት ራውል ካስትሮ ልዩ እንግዳና ተሸላሚው፣ ወደር የሌለው የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የጀግና ሜዳይ ተሸላሚው፣ ‹‹ሸንቃጣው፣ ሸቅርቅሩና መልከ መልካሙ›› የሚባሉት፣ የወይዘሮ አልማዝ አምሐ ባል፣ የነፃነት እና የሉሊት አባት፣ ጀግናው ብርጋዴር ጀኔራል ለገሠ ተፈራ የዚህ ሳምንት የታሪክ አካል ናቸው።

ከ51 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 26 ቀን 1966 ዓ.ም ‹‹የዮም ኪፑር›› ወይም ‹‹የረመዳን›› ጦርነት በመባል የሚታወቀው አራተኛው የዓረብ እስራኤል ጦርነት ተጀመረ።

ጦርነቱ በግብፅ እና በሶሪያ የሚመራው የዓረብ አገራት ጥምረት፣ በእስራኤል የዮምኪፑር በዓል ቀን፣ በእስራኤል ላይ ጥቃት ሲሰነዝር የተጀመረ ሲሆን፣ ውጤቱም የእስራኤልን አሸናፊነትና የዓረቦችን ተሸናፊነት ያሳየ ነበር። በአንዳንድ ተንታኞችም ግብጽ ከጦርነቱ መጠነኛ ጥቅም አግኝታለች ይባላል።

በዚሁ ቀን መስከረም 26 ቀን 1974 ዓ.ም የግብፅ ፕሬዚዳንት የነበሩት አንዋር ሳዳት ተገደሉ። ሳዳት የተገደሉት በመጀመሪያዎቹ ቀናት መጠነኛ ድሎችን ያገኙበትንና ከሞታቸው ቀን ልክ 8 ዓመታት በፊት የተጀመረውን የዮም ኪፑር ጦርነት 8ኛ ዓመት መታሰቢያ እያከበሩ ሳለ ነበር።

በካሊድ እስላምቡሊ የተመሩት የሳዳት ገዳዮች፣ ሳዳት ከዮም ኪፑር ጦርነት በኋላ ከእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኽም ቤጊን ጋር የተፈራረሙትን የካምፕ ዴቪድ የሠላም ስምምነትን አምርረው የተቃወሙ ፀረ እስራኤል አክራሪዎች ናቸው።

ከ9 ዓመታት በፊት መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም አንጋፋው ጋዜጠኛ፣ ዲፕሎማትና የታሪክ ጸሐፊ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ወልደአረጋይ አረፉ። አምባሳደር ዘውዴ ረታ ‹‹የኤርትራ ጉዳይ›› በሚለው ግዙፍ መጽሐፍ እና በሌሎች የታሪክ መጽሐፎቻቸው እንዲሁም በዲፕሎማትነታቸው ይታወቃሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ሶሬሳው

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

"ቦሄም አሰናናሁም!" ይላል ጉራጌ። እንኳን አደረሳችሁ! እያልኩ መኮላተፌ ነውና ... "ለምኑ?" ያላችሁ እንደሆን ለመስቀርና ልበል እንደጀመርኩት። "መስቀር መስቀር ቲሰራካ..." መግባባቱ አይሳነንምና መስቀል የመስቀሉ በዓል በደረሰ ቁጥር ሁሉ ... ሶሬሳው ቢሆን ኖሮ "ቤተና ሙራ" ባለኝ ነበር። የጎመን ድስት ወጥቶ የምንቸቱ መግባቱ መቼም ቤታችን ሙሉ ቢሆን ነው። "መስቀር ሰና ገኛይ አናርነዬ..." እንኂድ በማለት መስከረም ጠብታ ላደረሰችው የመስቀል በዓል በጉጉት ወደ ቀዬው እየገሰገሰ "የተንቢ!" ሲባል ለመስማት ይናፍቃል። ቀዬው እንደሆን በመስቀል ደስታ ነው። ፌሽታ ነው። የቤተ ጉራጌ ልጆች መስቀልን ወደ ቀዬ ሲሉ ከበሬው ቀጥሎ የማይዘነጓቸው ሦስት ልማዶች አሏቸው። አንደኛው መስቀልና ከእናት አባት ቤት መቅረት ነውር ነው። ሁለተኛው ለቤተሰቦቻቸው የሚሸከፉት ስጦታ ነው። ሦስተኛው ደግሞ የመስቀል ማድመቂያ የቴፕ ማጫወቻ ነው። እናም ከከተማ ቴፑን ገዝቶ፣ ሚሞሪውን አስጭኖ አልያም የካሴት አስቤዛውን አጭቆ ይገባል። በተለይ ወጣቱና ሕጻናት ልጆች ከሥራ ቀጥሎ ፍቅራቸው ለሙዚቃና የባሕል ጨዋታ ነው። ይህቺንም የሚያጣጥሟት በመስቀል በዓል ላይ ነው። በዚህ ውስጥም ከመስቀል ሙዚቃ ጋር ከፍ አድርገው በናፍቆት የሚያስታውሷቸው የሙዚቃው ባለቤቶች አሏቸው። እስቲ ማንን አስታወስክ ብላችሁ እያንዳንዱን ብትጠይቁ ውዱን ልጃቸው ሶሬሳውን ሳይጠቅስ የሚያልፍ አንድም አይኖርም።

"ዝ ሻዶ ሾርካ"፣ "የገንየ"፣ "ቤተና ሙራ"፣ "ህርም ህርም"፣ "ቲያርስና ዝሾታ"፣ "አትከታ የሟኒም አትከታ"፣"አርቴ ያዥመና"፣ "ኸጨዋ ገኘ ሰብ ጨዋ" እኚህና ሌሎችም የእርሱ መታወሻ የመስቀል መድመቂያዎቻቸው ናቸው። አንጋፋው የጉራጊኛ ሙዚቃ ድምፃዊ፣ እንዲሁም የግጥምና ዜማ ደራሲው ደምሴ ተካ (ሶሬሳ) ፍቅርና ክብር የሚደርቡለት ብዙዎችም "አጋዝ" ይሉታል። ይህን ታላቅ ስም ያሰጠው ሥራው ነው። መስቀር መስቀር ቲሰራካ...ደምሴ ተካን አለማስታወስ፣ ከዚም ከዚያም የቴፕ ድም! ድም! የእርሱን ድምፅ ሳይሰሙ ለሰዓታት እንደምን ተብሎ ይቻላል...ወደ የትኛው የቤተ ጉራጌ መንደር ቢያቀኑ በመስቀል ያለ ሶሬሳው ደምሴ ተካ ሙዚቃዎች ቢላው እንኳን ለአራጁ አይታዘዝም። በሠርግ ከሚዜው እስከ ሠርገኛ፣ ሙሽራና ሙሽሪት "ሀይ ሎጋ ሆ ምሽራ ሀይ ሎጋ ሆ..." የምትለዋን ድምፀ ቅላፄውን ካልሰማ በስተቀር ሠርጉም ሠርግ አይመስለው። "ሀይ ሎጋ ሆ" አንዷት ነጠላ ዜማ ብቻ ሳትሆን ከሀገር ምድሩ ጋር የተዋወቀባት ምርጥ የካሴት ሥራው ናት። እስካሁን ከአሥር በላይ የሆኑ አልበሞችን በመሥራት የማይነቀነቅ የባሕል ምሰሶ ሆኗል።

ደምሴ ተካ የተወለደው በ1960 ዓ.ም በኸዣ ወረዳ ውስጥ ነበር። ከዚህ በኋላ ደምሴ አዲስ አበባን ለመርገጥ የፈጀበት ሰባት ዓመታት ብቻ ነበሩ። ደምሴ 12 ዓመት ሲሞላው ያመራው ወደ መርካቶ አልነበረም። በአጎቱ መሪነት በቀጥታ ወደ ደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አምርቶ ድቁና ላይ ደረሰ። በድቁናው ሳለም 1979 ዓ.ም በሀገራዊ ግዳጅ ወደ ብሔራዊ ውትድርና ገባ። የገባበት የባሩድ ሜዳ ግን እንዲሁ እንደዋዛ የሚያልፈው አልነበረም። ፈታኙን የሥልጠና አጥር እየዘለለ በሄደ ቁጥር ሰውነቱ ከሕመም ጋር መፋተግም ጀመረ። የወታደርነቱ ካባ አልሆንህ እያለው ከውስጡ ጋር ብዙ እሰጣ አገባ ውስጥ ሳይገቡም አይቀርም። በዚያ የጦር ደጃፍ ላይ እያለ ጠላትን ከጠመንጃ ይልቅ በድምፅ የሚማርክ ዓይነት መሆኑን ያወቁለት ቀላል አልነበሩም። ከመውዜሩ ቃታ የሙዚቃውን ማይክ ቢጨብጥ የተሻለ አበርክቶ ሊኖረው እንደሚችል መቼም አለቆቹም ያወቁት ይሆናል።

ደምሴ ድምፁ ለሙዚቃ የሰጠ ነበር። በኋላ ላይ ተመልሶ አዲስ አበባ ላይ ተገኘ። እንደተመለሰም ሆነ ከተመለሰ በኋላ የእርሱ ሀሳብ ሙዚቃ ላይ አልነበረም። ሲያስብ ሲፈልገው የነበረው ቀደም ሲል ጥሎት የሄደውን ድቁና ነበር። ሊሆንለት ግን አልቻለም። ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ተመልሶ ደጅ ሲጠና ከአንድ ዓመት በላይ ለደርግ መንግሥት በውትድርና ያገለገለ ተመልሶ ለድቁናው አይታጭም ተባለ። ግራ የገባው ደምሴም ቀድሞውኑ ወደ ውትድርናው ዓለም ወደ ላከው አጎቱ ሄዶ ሁኔታውን ነገረው። አጎትም ለዛሬው ደምሴ ፍኖት ለመሆን ወደ በቃውና የቲያትር ባለሙያ ወደ ሆነው ጀንበሬ በላይ ዘንድ አቅንቶ ጉዳዩን አጫወተው። በኔ ጣለው ያለው ጀንበሬ በላይም ደምሴን ይዞ ወደ ብሔራዊ ቲያትር ወሰደው። ሲደርስም እርሱን ሲጠብቅ የነበረ ይመስል በጊዜው በድምፃዊነት ሲያገለግሉ የነበሩ አንድ ሰው በጡረታ ተገልለው ቦታው ክፍት ነበር። ፈታኞች ፊት ለፈተና የቆመው ደምሴ ተካም "ጀማዬ ነይ ነይ፣ ጀማዬ ነይ ነይ.." እያለ ቢዘፍን ጊዜ፤ ትፈለጋለህና አንተም ና! ተብሎ ከዚያው ቀረ። በፈተና ሰዓት ከ"ጀማዬ" አስከትሎ የተጫወተው "ሌዎሌ" የተሰኘው የተሾመ ወልዴ ሙዚቃ፤ ዜማና ግጥሙን ሠርቶ የሰጠው ራሱ ደምሴ ተካ ነበር።

ከአዲስ አበባም ወደ ብሔራዊ ቲያትር እያንኳኳ ገብቶ ለመቀጠር ቻለ። በብሔራዊ ቲያትር መድረኮች ላይ ድምፁን እያስረቀረቀ በጉራጊኛ ሙዚቃዎቹ ምርኮኛዎቹን ሲያበዛ የተመለከተው መልካሙ ተበጀ ሌላ መንገድ አስመለከተው። አልበም ቢሠራ የተሻለ መሆኑን ከምክር ቢጤ ጋር ጣል አደረገለት። የመልካሙ ተበጀ ቃላት በወኔ ያጋሉት ደምሴ ተካም ዓይኑን ሳያሽ ወደ መርካቶ ገሰገሰ። ከሙዚቃ ቤት ወደ ሙዚቃ ቤት፣ ከአንዱ አሳታሚ ወደ ሌላው እያለ ለሥራው ሰው ፍለጋ ብዙ ኳተነ። የካሴት አልበሙን ሊሠራለት ተስማምቶ ሙዚቃዎቹን የተቀበለው አንዱ ባለሙያ፤ ተቀብሎ ስድስት ወር ያህል ከጎለታቸው በኋላ መልሶ ሀሳቡን ቀየረ። ተስፋ ያልቆረጠው ደምሴ እንደገና ለሌላኛው ሰጠው። 12 የጉራጊኛ ሙዚቃ ሳምፕሎችን ሰጥቶ በሌላኛው ጊዜ ለምላሹ ሲመጣ፤ ከሦስቱ በስተቀር ሁሉም ሙዚቃዎች በሌላ መቀየር አለባቸው ሲል ከመርዶ ያልተናነሰውን ምላሽ ሰጠው። ፈተናው አለቅህ ብሎ አንገት የተናነቀው አልበም አሁንም ወደ ሦስተኛው ሰው ተላለፈ። ግን ሦስተኛውም ከእጅ አይሻል ዶማ ሆነ። አንድ ዓመት ያህል ካቆየው በኋላ፤ ማስተሩን የሚሠሩት እነ እገሌ ወደ አሜሪካን ስለሄዱ እስኪመለሱ ለስድስት ወር ያህል ጠብቅ የሚለውን ምላሽ ሲሰማ ግን እልህና ንዴት እየተናነቀው ከዚህ ቀደም ሠርቶለት ወደ ነበረ ሰው ተመለሰ። ወለል ያለችውን የሙዚቃ ስኬት ጎዳና የረገጠው ከዚህ ሁሉ የአሳር ቁጥቋጦና ጥሻ ውስጥ አምልጦ ነበር።

እንዲያው ጥቂት አክሮባት ሠርተን ወደ ኋላ ምልስ ስንል ደምሴ ተካ ምንም እንኳን ድቁናውን ይዞ ስለመቀሰስ እያሰበ የነበረ ቢሆንም አንድ ያላስተዋለው ነገር ነበር። ምንም ማርከሻ የማይገኝላት የሙዚቃ ንብ እዝዝ! ጥዚዝ! እያለች ከአናቱ ላይ እየሾረች ትርኩስ አድርጋ የነደፈችው ገና ያኔ ጨቅላ ሳለ ነበር። እስከ ሰባት ወይም ስምንት ዓመቱ ድረስ የነበረው ክፍለ ሀገር እንደመሆኑ በውል ያላስተዋላቸው ጥቂት የመስቀል በዓልና ሠርጎችን ታድሞ ጨፍሮባቸዋል። ታላላቆቹ ከበሮ እየመቱና ግጥም ዜማ በድምፅ እያወጡ ሲጫወቱ ተከትሏቸዋል። በአንድ የጉራጌ መንደር ውስጥ ልጆች ከልጆች ጋር ሰብሰብ ብለው ከአቻዎቻቸው ጋር እንዳሻቸው እንዲጫወቱ ነፃነት የሚነፍጋቸው የለም። በዝግጅቶች ላይም ቢሆን የአቅማቸውን ቢጨፍሩ ቢያዜሙ ማንም "እረፉ" እያለ የሚያስደነግጣቸው አይኖርም። ማራኪውን የባሕል አጨፋፈር ስልትና የሙዚቃን ጣዕም የሚያጣጥሙት በዚህ የልጅነት ነፃነት ውስጥ ነው። ደምሴ ተካም የተመለከቱትን ሁሉ መሞከር ደስ በሚያሰኘው ዕድሜ ውስጥ ሆኖ በትንሹም ቢሆን ከመንደሩ ልጆች ጋር ይህን ተጋርቷል። እንደ አብዛኛዎቹ ልጆችም በዚያ ጨቅላነት ስለ ሙዚቃ ሳያውቅ ሙዚቃ ግን ነድፋው ነበር። ሳይረዳው የቆየውም ያንን ጊዜ ነው። ግን የያዘ አይለቅምና ምን ቅስና ምን ጵጵስና ቢመኝም ውስጡ በማያውቀው ነገር ሲንቀለቀል ዘግይቶ ይሰማው ጀመረ።

በወቅቱ ሲያገለግል ከነበረበት ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የ08 ቀበሌ ከፍተኛ የኪነት ቡድን ነበር። ደምሴ ደግሞ ማታ ማታ ትምህርቱን ይከታተል ነበር። ከትምህርት ቤት ጨርሶም ሆነ ሾልኮ እየወጣ የሚፈረጥጠው ወደ ቤት ሳይሆን ወደ'ዚያ የቀበሌ ኪነት ነበር። ድቁናውን በማዕረግ ሙዚቃን በልቡ ይዞ የኪነት ቡድኑን ሲመለከት የማምሸቱ ነገር ከቤተ ክርስቲያን አባቶቹ ጆሮ ደርሶ፤ ኧረ እባክህን አንተ ልጅ! ታስወቅሰናለህ... እዚህ ጊዮርጊስ እየቀደስክ እንደገና እዚያ ልትዘፍን ነው...ቢሉ፣ ቢመክሩት አንድ ጊዜ ተይዟልና ወይ ፍንክች አለ። ይባስ አብሮ ልምምድ ሁሉ ማድረግና መዝፈኑን ጀመረ። የሙዚቃ ስሜቱ ወደ ጡዘት እያሻቀበ ግጥምና ዜማ ሁሉ መድረስ ጀማመረው። ከዚያን ወዲህ የሚያቆመው አልተገኘም። ከሠራቸው ግጥሞች መካከልም አንዱን ለተሾመ ወልዴ አቀበለው። ቀጥሎም ወደ ደምሴ የመጣው ኬኔዲ መንገሻ ነበር። "ሙናናዬ" የሚለውን ግጥምና ዜማ ተቀብሎ ኬኒዲ በመጀመሪያው አልበሙ ውስጥ አካቶታል።




በአቀበት ቁልቁለቱ ሲጓዝ ሙዚቃን ከመሥራትም አልፎ አንጋፋዎችንም ሲያሠራ ብዙ የተጓዘው ሶሬሳው በብሔራዊ ቲያትር ውስጥ ቆይታው የድምፃዊነት ብቻ አይደለም፤ ጎን ለጎን በተለያዩ ውስጣዊ ኃላፊነቶች ውስጥም ትልቅ ሚና ሲጫወት ቆይቷል። የጉራጊኛን ሙዚቃ የሚያዳምጡና ቋንቋውን የሚችሉ ብቻ ሳይሆን እንዲሁ በአጋጣሚዎች ስለ እርሱ የሰሙ ሁሉ አድናቂዎቹ ናቸው። የጉራጌን ባሕልና ሙዚቃ ከፍ አድርጎ በማስተዋወቅ ደረጃ ሶሬሳውን የሚስተካከል ሙዚቀኛ አለ ለማለት ያዳግታል። ከእርሱ በኋላ ለመጡ ለበርካታ የጉራጊኛ ሙዚቀኞች ጥላ ከለላ ሆኗቸዋል። መቼም የማይዘነጉትን የጥበብ መንገድ መርቶ አሳይቷቸዋል። በርካታ ሙዚቀኞችም የሙያ አባታቸው አድርገው ተቀብለውታል። ለአብነትም ተወዳጁ ኃይሉ ፈረጃና ሞክሼው ደምሴ መርሻ በሙያው ውስጥ የሰጣቸውን በልተው፣ የነገራቸውን ሰምተው ያደጉ የአባታቸው ልጆች ናቸው። ደምሴ ተካ ዛሬ ላይ የጉራጊኛ ሙዚቃ የባሕል አምባሳደር ነው።

ሶሬሳው በጉራጊኛ ሙዚቃ ውስጥ ከብዙዎች ለየት የሚያደርገው አንዲት ነገርም አለችው። ሁሉም ጉራጌ፣ ሁሉም ጉራጊኛ ቢሆንም ቋንቋ ግን ልዩ ኅብርን ይዞ በየአካባቢው የሚነገርበት ዘዬ የተለያየና ከአንዱ የሌላው ወጣ ያለው ነው። ደምሴ ተካም በአንዱና በተመቸው ብቻ ሳይገታ ከክስታኔ እስከ እንደጋኝ፣ ከምሑር እስከ እኖርና ሌሎችም ድረስ በመዝለቅ ከግማሽ በማይተናነሱት ዘዬዎች ሁሉ ሙዚቃ አበርክቷል። ወደ የትኛዎቹም ቤተ ጉራጌዎች ጎራ ቢሉ ደምሴ የሁሉም የልብ ትርታ ነው።

በጉራጊኛ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ጥበብ ከፍላ የማትጨርሰውን ውለታ በመዋል አልበሞች በማይወጡበት ጊዜ ሁሉ አድማጩ ፆም ውሎ እንዳያድር እያከታተለ አጥግቦታል። በተለይ ደግሞ ከ1985 እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ ድረስ በነበሩት ጊዜያቶች ያበረከተው እድሜ ዘላለሙን እጁን የሚያስም ነበር። በሠራቸው አሥር አልበሞች ውስጥ ያላነሳው የሀሳብ ቅርንጫፍ፣ ያላበላው የዜማ ትርንጎ የለም። ምግባረ ፀዓዳ፣ ደመ ግቡ የሀገር ፍቅር የተሸከመ ስለመሆኑ እልፍ ምስክር ቢኖረውም ምስክር ግን አያሻውም "ኢትዮጵያ አዶተና" ይላታል ሀገሩን። በብስል ትርጓሜው "እናት ኢትዮጵያ" እንደማለት ነው። ደግሞ "ንዝግድና" ያላት እናትና "አባና" ያለው አባትም አለው። ከሥራ መሐል ተወልዶ፣ በሥራ የኖረ ትጋት አይለዩ እጹብ ማንነት አለውና "ቶቺ ሜና" ሲል የደከመን በወኔ፣ ብርቱውን ወደ ፊት በዜማ ያሰልፈዋል። ከሀገር ባሕል፣ እስከ ኑሮ ዘንቢልና ፌስታል ብቻ በዚያ ስርቅርቅ ድምፁ ያልገባበት የለም። ሲያደምጡት በጆሮና ልብ ስበት የሚማርከው ድምፁ በቴፕና ማጫወቻዎች ውስጥ ቢሆን መድረክ ላይ ፈጽሞ አይለዋወጥም። ተፈጥሮ በጥበብ የቸረችው ነውና በየትኛውም ጊዜና ቦታ ቢሆን እንደ አንዳንዶች የሚያሳብብበት ጉንፋን የለም።

ሙዚቃ በደምሴ ተካ ሕይወት ውስጥ ለጥሪ ነብስያው ማረፊያ ከመሆኗም ለኑሮውም መግፊያ ጭምር ናት። ባገኘው የሥራ አጋጣሚ ሁሉ በሠርጎች ላይ እየተገኘ በሠርግ ሙዚቃዎቹ እያደማመቀ አቧራ ሲያስጨስ ይኖራል። በአንድ ወቅት ታዲያ አንድ ሰው ደውሎ በቅርቡ ከውጭ ሀገር መጥታ የምታገባ እህት አለችኝና ተሰናዳ በማለት ይነግረዋል። ሠርጉ የሚካሄደው የትና በምን መልኩ ነው የሚለውን በስልክ ካወጉ በኋላ፤ ለሥራው ቀብዱን የሚከፍልህ አባቴ ነውና እቤት እንድትመጣ በማለት አድራሻውን ሰጠው። ደምሴም ስምምነቱን ለመፈጸም በቀጥታ ወደ ተነገረው ቤት አመራ። በወግ ተቀብለው ከቤት ከገባ በኋላ ምሳ በላ። ጠጣ። ወደ መጣበት ጉዳይ ሲገባም "አባዬ ያው እንግዲ ደምሴ መጥቷል። በቀደም የነገርንህን ነገር ውሉን ይዟልና ቀብዱን ስጠው" ሲሉ ልጆች ለአባታቸው ይነግሯቸዋል። አባትም "የቱ ነው ደምሴ?" ይላሉ። "ዘፋኙ ደምሴ" አባት አሰብ አደረጉና "አላወቁትም" አሉ። ልጆቹም ቤቱ ውስጥ በየፊናው ፈለግ ፈለግ አድርገው የደምሴን ሙዚቃዎች እየከፈቱ አንድ ባንድ አስደመጧቸው። "አሃ! 'ያሆ ጃማ' የሚለው ልጅ ነው እንዴ" በማለት ያስታወሱት እየመሰሉ "እና ደምሴ ማለት ይኼ ነው?" "አዎን አባዬ" አሉ ልጆቹ በአንድ ድምፅ። "አይ ደምሴን አውቀዋለሁ ይኼማ እሱ አይደለም። በፎቶ አይቼዋለሁ" በማለት ፈርጠም ብለው አስወጡልኝ አሉ። "ኧረ አባዬ እሱ ራሱ ነው" በማለት በዚህ ቢሉ በዚያ "ዝም በል! ሌባ ተመሳጥራችሁ ገንዘቤን ልትበሉ ነበር! አስወጡልኝ!" ብለው እርፍ! በገዛ ማንነቱ ላይ አንተ አይደለህም ተብሎ ቅንጡን የተመታው ደምሴም እግሬ አውጪኝ ሲል ጥሎ ሄደ።

ሙዚቃ ሕይወት ነው። ሕይወት ደግሞ በውጣውረዶች የታጀበች ትናንት፣ ዛሬና ነገ ናት። ዛሬ ላይ ድንገት ጥቁር ደመና ክልብስ! ሲል ብልጭ የምትል የነገ ተስፋ ደርሳ ታነሳናለች። ለሶሬሳው ደምሴ ተካ ሕይወት የሥራውን ያህል ቀላል ሳትሆንለት ቀርታለች። ዘጠኝ አልበሞችን ከሠራ በኋላ በተደጋጋሚ የሚገጥሙት ነገሮች ትክት ስልችት ቢሉት ጊዜ ከእንግዲህስ አልበም አልሠራም በማለት ለይፋ የተቀራረበ ንግግር አደረገ። የኮፒራይት ጉዳይ እጅግ እንዳንገሸገሸው አልደበቀም ነበር። በቃ ከእንግዲህ አዳዲስ አልበሞቹን ላናደምጥ ነው በማለት ንግግሩን የሰሙ ብዙዎች ተስፋ ቆርጠው ነበር። ነገር ግን ከድቁናው ለይቶ ቅስናውን ያስመለጠው ውቃቤ ሙዚቃ በሀሳብ ቀርቶ መች በፀበልስ የሚለቅ ሆነና... በ2014 ዓ.ም "ሰበና" ሲል አሥረኛውን አልበም በማስደመጥ ሌላ የሙዚቃ ካብ ካበና ተካበ። በጉራጊኛ የአልበም ታሪክ በአሥር የነገሠ የመጀመሪያው በመሆን የንግሥናውን ዘውድ ደፋ። ረዥም እድሜን ከጤና ጋር ለሶሬሳው የጥበብ ልጅ!!

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ የትራምፕ የምርጫ ዘመቻ መረጃን መንትፈዋል ያለቻቸውን ሦስት ኢራናውያን ከሰሰች

አሜሪካ ከዶናልድ ትራምፕ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ቅስቀሳ መረጃዎችን ከመመንተፍ ጋር በተያያዘ ሦስት ኢራናውያን ላይ ክስ መሰረተች።አቃቤ ሕግ የኢራን እስላማዊ አብዮት ዘብ አባላት ናቸው ያላቸውን ማሱድ ጃሊል፣ ሰይድ አሊ አግሃሚሪ እና ያሳር ባላጋሂ "መረጃ በመመንትፍ እና ሰነድ በማሹለክ" ተግባር ላይ "ይኹነኝ ተብሎ" በስም ያልተጠቀሰን የምርጫ ዘመቻ ለማጣጣል ሲሰሩ ነበር ብሏል።

ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ ባለስልጣናት የኢራን መረጃ መንታፊዎች ከዶናልድ ትራምፕ የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪዎች የወሰዱትን ሰነድ ከባይደን የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪዎች ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች መላካቸውን ገልጸው ነበር። ሦስቱ የመረጃ መንታፊዎች የተከሰሱት በ18 ወንጀሎች መሆኑ ተገልጿል።

በነሐሴ ወር ላይ የትራምፕ ምርጫ ቅስቀሳ ቡድን የውስጥ ግንኙነት ልውውጡ በኢራን መረጃ መንታፊዎች መሰረቁን ገልጾ ነበር። በወቅቱ የኢራን ባለስልጣናት በመረጃ ምንተፋው ላይ እጃቸው እንደሌለበት በመግለጽ አስተባብለዋል። ከጥቂት ቀናት በኋላ የፌዴራሉ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ወደ ትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ኢራን ሰርጋ መግባቷን አረጋግጧል።

የአሜሪካ የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ ባለፈው ነሐሴ ወር ላይ ኢራን በመጪው የአሜሪካ ምርጫ ላይ ክፍፍልን ለመፈጠር እንዲሁም ዜጎች በአሜሪካ መንግሥታዊ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት እንዲሸረሽር ለማድረግ እንደምትጥር አስጠንቅቆ ነበር። ባለሥልጣናቱ ኢራን ይህንን ዓላማዋን ለማሳካት እና የዲሞክራቶች እንዲሁም የሪፐብሊካኖች የምርጫ ማስተባበሪያዎችን በቀጥታ ለመበርበር "ማኅበራዊ ምህንድስና" የተባለ እና ሌሎች ስልቶችን ስትጠቀም ነበር ብለዋል።

ይህንን ስልት ኢራን እና ሩሲያ በሌሎች አገራት ላይ የሚተገብሩት እንደሆነም አንስተዋል። ቢሮው አክሎም "በዚህ የምርጫ ወቅት ኢራን ይህንን ድርጊቷን በስፋት እንደቀጠለችበት ይታያል" ሲል አስጠንቅቋል። 37 ገጽ የያዘው የመረጃ መንታፊዎቹ ክስ ዝርዝር እኤአ ከ2020 ጀምሮ ከፖለቲካ ምርጫ ጋር ተያይዞ የአሜሪካ መንግሥት፣ የደህንነት ባለስልጣናትን፣ መገናኛ ብዙኃንን፣ እንዲሁም ከምርጫ ቅስቀሳ ጋር የተገናኙ ግለሰቦች ላይ ትኩረት አድርገው ሲሰሩ ነበር ይላል።

በ2024 ግንቦት ወር ላይ የፍትህ ቢሮ ሦስቱ መረጃ መንታፊዎች "የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ 1" ላይ ትኩረት በማድረግ ማሴር ጀምረዋል ሲል ይወነጅላቸዋል። ተጠርጣሪዎቹ በምርጫ ዘመቻ ላይ የሚሳተፉ ግለሰቦችን ኢሜል ለማግኘት በሚል ሀሰተኛ የሆነ አድራሻ በመጠቀም እና ራሳቸውን የአሜሪካ ባለስልጣን በማስመሰል ሰነዶችን እና የመረጃ ልውውጦችን ሰርቀዋል ሲል ወንጅሏቸዋል።

በሰኔ ወር ላይ ደግሞ የተሰረቁትን መረጃዎች ለመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም "ከአሜሪካ ምርጫ ዘመቻ 2" ጋር ለተገናኙ ሰዎች በማሹለክ "እንደ መሳሪያ ሊጠቀሙበት" መሞከራቸውን ጠቅሶ ይከስሳቸዋል። ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ አንቶኒ ሜሪክ ጋርላንድ የባይደን የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን መረጃዎቹን ተጠቅምባቸው እንደሆነ ተጠይቀው " ምንም ዓይነት ፍንጭ አላገኘንም" ሲሉ መልሰዋል።

እንዲሁም ኤፍቢአይ ከትራምፕ እንዲሁም ከባይደን በኋላም ካማላ ሃሪስ ከተረከበው የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን አባላት "ጥሩ ትብብር" ማግኘቱን ገልጸዋል።የካማላ ሐሪስ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን አስታውቋል።

"ምንም ዓይነት ሰነድ በቀጥታ ለቅስቀሳ ዘመቻው መላኩን አናውቅም፤ የተወሰኑ ግለሰቦች በግል የኢሜል አድራሻቸው አሳሳች መልዕክቶች የሚመስሉ ተልኮላቸዋል" ብለዋል የካማላ ሐሪስ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ፀሀፊ ቃል አቀባይ ሞርጋን ፊንክልተይን።



የክሱ ዝርዝር እንደሚያ ስረዳው ከሆነ "የቀድሞ፣ መደበኛ ያልሆ ኑ የትራምፕ የፖለቲካ አማካሪ" ኢሜል በዚህ የመረጃ መንታፊዎች መረብ ውስጥ ወድቋል። እንዲሁም ስሙ ያልተጠ ቀሰ በምርጫ ዘመቻው ላይ ተሳትፎ ያለው ኃላፊ እና እርሱን የሚወክል ጠበቃ ኢሜልም እንዲሁ በመረጃ መንታፊዎቹ እጅ ገብቶ ነበር። የኤፍ ቢአይ ዳይሬክተር ክርስቶፈር ውሬይ በመግለጫቸው ላይ"ዛሬ ለኢራን መንግሥት ኤፍ ቢአይ መላክ የሚፈልገው መልዕክት እናንተ እና መረጃ መነታፊዎቻችሁ ከኮምፒው ተራችሁ ጀርባ ተደብቃችሁ አትቀሩም የሚል ነው" ብለዋል።

በተጨማሪም ክሶቹ "ኤፍ ቢአይ ለረዥም ጊዜ ክትትል ያደረገባቸው እና በሚገባ ያደራጀው ማጠቃለያ የቀረበበት ነው" ብለዋል። ኢራን በእጇ አስገብታዋለች ከተባለው ሰነድ መካከል ከፕሬዚዳንት ትራምፕ ጋር ለምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩት እጩ ጄዲ ቬንስ መረጃዎች ናቸው።

እነዚህ ሰነዶች እና ሌሎች መረጃዎች ለበርካታ የአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን የተላኩ ሲሆን፤ በስፋት የተሰራጩት ግን ሐሙስ ዕለት ኬን ክሊፔኒስቴይን የተባለ ጋዜጠኛ በግል ጦማሩ ላይ ካጋራቸው በኋላ ነው። ክሊፔይንስቴይን "ሮበርት" የተባለ ግለሰብ ሰነዶቹን እንደላከለት የገለጸ ሲሆን፤ ወዲያውኑ ከኤክስ ገጹ ላይ ታግዷል። ኤክስ ባወጣው መግለጫም የግለሰብን መረጃ ይፋ በማድረግ ላይ ያለውም መመሪያ ጥሷል ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ማስታወቂያ

ስማቸው ከታች የተዘረዘሩት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሚኖሩበት ወረዳ ቀርበው ባለትዳር መሆናቸውን አስመዝግበው የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ጋብቻ የሌላቸው አልያም የትዳር አጋር ያልነበራቸው መሆኑን በማስረዳት የፍ/ቤት ውሳኔ /ተጠሪ ባይኖርም/ ይዘው በመቅረብ ያላገባ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ተቋማችንን የጠየቁ በመሆኑ ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር ጋብቻ ነበረን ወይም በአሁኑ ወቅት በጋብቻ ውስጥ ነው ያለነው የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ የኤጀንሲው ዋናው መ/ቤት በአካል በመቅረብ ሪፖርት እንድታደርጉ እናሳውቃለን፡፡

ከቀነ ገደቡ በኋላ የሚመጣ ማንኛውም አይነት ጥቆማ ተቀባይነት የሌለው እና ኤጀንሲው በፌዴራል የቤተሰብ ህግ እና በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነት ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 145/2015 መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥበት ጭምር መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | አድራሻ | | ያስመዘገቡት የጋብቻ ዓይነት | ያስመዘገቡት የትዳር አጋር | የፍ/ቤት ተጠሪ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክ/ከ | ወረዳ | | | |
| 1 | ሰውዓለም መብራቱ መልካሙ | የካ | 12 | ባህላዊ | ወርቅነህ ፈረደ | የለም |
| 2 | ብዙነሽ አስፋው ደመቀ | የካ | 5 | ባህላዊ | ግርማው ከበደ | የለም |
| 3 | ገነት ድንቁ ጋሜ | ኮ/ቀራንዮ | 1 | ፍቺ | ጫኑ ሀብቴ | |
| 4 | ሻማ ብሩ ሰንበታ | የካ | 6 | ባህላዊ | አበራ ፈይሳ | የለም |
| 5 | ፀሐይ ሞላ ዮሴፍ | የካ | 7 | ባህላዊ | ሰለሞን ከበደ | የለም |
| 6 | ትዕግስት በየነ አርአያ | የካ | 5 | ያላገባች | | የለም |
| 7 | አበባ በቀለ ታፈሰ | ቦሌ | 6 | ብሔራዊ | ያለው ወንድም | የለም |
| 8 | ቅድስት መንግስቱ ደስታ | የካ | 1 | ባህላዊ | ሲሳይ ወርቁ | የለም |
| 9 | ሰላም ገብሩ አብርሃም | የካ | 7 | ባህላዊ | ሰለሞን መካሻ | የለም |
| 10 | ፊትለወርቅ በዕደ መላኩ | የካ | 7 | ባህላዊ | ሰለሞን አባቴ | የለም |
| 11 | ምስራቅ እንዳለ በዳኔ | ኮ/ቀራንዮ | 4 | ብሔራዊ | አበበ መኩሪያ | የለም |
| 12 | ነፃነት ጌታቸዉ ጅማ | የካ | 7 | ባህላዊ | ልዑል አበራ | የለም |
| 13 | ባዩሽ አበባዉ መጨ | ጉለሌ | 7 | ያገባች | ነጋሽ አበበ | ነጋሽ አበባ |
| 14 | የሺ ቱፋ ተሊላ | የካ | 5 | ፍቺ | የለም | የለም |
| 15 | ቅድስት ፀሐይ ጉርሙ | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 3 | ባህላዊ | ፍቃዱ ጥላሁን | ፍቃዱ ጥላሁን |
| 16 | ገላኔ ጉታ ቁንቢ | የካ | 8 | ባህላዊ | እንዳሻው ደሳለኝ | እንዳሻው ደሳለኝ |
| 17 | ንፁህ ገሰሰ መከብብ | የካ | 8 | ባህላዊ | ተስፋዬ ካሣዬ | የለም |
| 18 | ሞሚና ሙስጠፋ አሊ | ቦሌ | 14 | ፍቺ | | የለም |
| 19 | ወርቅሸት አለማየሁ በላይነህ | ቦሌ | 14 | ባህላዊ | ጥላሁን ፍቃዱ | የለም |
| 20 | ፅጌ ተስፋዬ ተክለወልድ | የካ | 8 | ባህላዊ | ቢያኒያም ወንዶሰን | የለም |
| 21 | አለማሽ ገ/ፃዲቅ ሳቦ | ልደታ | 8 | ያላገባ /ፍቺ/ | ዘራያ አበበ | የለም |
| 22 | ተረፉ ቦጋለ ካሣ | ንፋስ | 12 | ያላገባ /ፍቺ/ | የለም | የለም |
| 23 | መድሃኒት መንግሥቱ ተሰማ | የካ | 5 | ባህላዊ | የትዳር የለም | ----- |
| 24 | እታበዛሁ ለገሰ ፈንታ | አቃቂ ቃሊቲ | 1 | ብሔራዊ | በቃሉ አገኘው | ------ |
| 25 | ትዝታ ጋሻው አዲሴ | የካ | 9 | ባህላዊ | የኔነህ የኋላሸት | --- |
| 26 | ደጅይጥኑ ገረመው መስፈን | ጉለሌ | 3 | ባህላዊ | አብርሃም በላይ | --- |
| 27 | ራሄል በላይነህ አበበ | የካ | 10 | ባህላዊ | ተስፋ | --- |
| 28 | ሰናይት ዳምጠው ዳጄ | ኮልፌ | 10 | ባህላዊ | ሰለሞን ኃይሉ | -- |
| 29 | ጋሜቲ ገዝሙ ጅማ | የካ | 5 | - | የለም | የለም |
| 30 | ዘነበች ኃይሌ ጉልማ | የካ | 5 | - | -- | --- |

➢ አድራሻ፡- አዲስ አበባ ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ልዩ ስሙ አዲሱ ገበያ ሸገር መናፈሻ

➢ ነፃ የስልክ መስመር፡- 7533

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
እሁድ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ከታላላቅ ውድድሮች በኋላ የአትሌቶች ስሜት መረበሽ

**ብርሃን ፈይሳ**

እንደ ኦሊምፒክ ያሉ ታላላቅ ውድድሮች ከመሄዳቸው አስቀድሞ በአትሌቶች ዘንድ ጠንካራ ዝግጅት ማድረግ የተለመደ ነው። በጠንካራ ተፎካካሪነት ሰንደቅን ለማስከበር በአካልና በአዕምሮ ይተጋሉ። በውድድሩ ወቅትም የተቻላቸውን በማድረግ እንዳለሙት ሜዳሊያ ሊያሳኩ ወይም በተለያዩ ምክንያት የተጠበቀው ውጤት ላይገኝ ይችላል። ከሳምንታት ደማቅ የኦሊምፒክ ቆይታ በኋላም ወደየሃገራቸው የመልስ ጉዞ ያደርጋሉ። እንዳገኙት ውጤትና አስቀድሞ ቃል በተገባላቸው መሠረትም በአቀባበል፣ በሽልማት እንዲሁም በተለያዩ መድረኮች እየተገኙ ልምዳቸውን በማካፈል መርሐ ግብር እንደተጠመዱም ሞቅታው ለተወሰኑ ቀናት ይቆያል። ከዚያ በኋላስ የአትሌቶች ሕይወት በምን መልኩ ይቀጥላል?

ለረጅም ወራት የሚኖረው ከባድ የዝግጅት ጊዜ እና ውድድር እጅግ አድካሚ በመሆኑ ተገቢውን እረፍት ማድረግ የግድ ነው። ነገር ግን በዚህ የእረፍት ጊዜ አትሌቱ በአካልና በአዕምሮ ሠላማዊ ጊዜን አሳልፎ ለቀጣዩ የውድድር ዘመን ራሱን ያበቃል? ይህ ሁኔታ በእርግጥም ከስፖርት ቤተሰቡ የራቀ በባለሙያዎች ዘንድ ግን የታወቀና በእጅጉ እገዛ የሚያስፈልገው ድምጽ አልባ ችግር ነው። ምክንያቱ ደግሞ በውድድሩ እና ውድድሩን አስቀድሞ የነበሩ እንቅስቃሴዎች መቋረጣቸው አትሌቶችን ከእረፍት ይልቅ ለስሜትና አእምሮ መቃወስ የሚዳርግ በመሆኑ ነው።



በበርካታ የስፖርት ቤተሰብ ዘንድ እምብዛም የማይታወቀው የአትሌቶች የስሜት ለውጥ ‹‹ፖስት ኦሊምፒክ ብሉስ›› በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን፤ ከውድድር በኋላ በሚኖሩት ጥቂት ቀናት አሊያም ሳምንታት ሊከሰት ይችላል። ይኸውም ድብርትን፣ ግራ መጋባትን እንዲሁም ስለራስ አሉታዊ አስተሳሰብን ወደማዳበር የሚከት ነው። ጉዳዩ የሚከሰተው ውጤታማ በሆኑትም ሆነ ባልተሳካላቸው አትሌቶች ላይ መሆኑ ደግሞ ጉዳዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያመላክታል።

በቅርቡ በተካሄደው የፓሪስ ኦሊምፒክ በሴቶች 800 ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀችው እንግሊዛዊቷ ኬሊ ሆድሰን ፋይናንሺያል ታይምስ ከተሰኘው ጋዜጣ ጋር በነበራት ቆይታ ልምዷን አካፍላለች። ከውድድር ውጪ በምትሆንበት ወቅት የጊዜው መርዘም እንዲሁም ቀጣይ ሁኔታን ማሰብ ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ ግራ መጋባት ውስጥ እንደሚከታት ነው ያንፀባረቀችው። በዲስከስ ውርወራ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የሆነችው ሌላኛዋ አትሌት ቫለሪ አለምን በበኩሏ ‹‹ስለ ኦሊምፒክ ማሰብ አትሌቶችን በክብር ብቻም ሳይሆን እንደ ልብ መሰበር ያሉ የተለያዩ ስሜቶችን እንዲያስተናግዱ ያደርጋል። በመሆኑም እርስ በእርስ ሃሳብን መካፈል የሚኖረውን ግፊት ሊያስቀር ይችላል›› ስትል ትጠቁማለች።

ዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጉዳዩ ላይ ባካሄደው ጥናት መሠረት ሁኔታው 35 ከመቶ የሚሆኑ አትሌቶች ላይ ሊደርስ የሚችል መሆኑን አረጋግጧል። የስፖርት ሥነልቦና ባለሙያዎች አስፈላጊነትም በውድድር ወቅት የአትሌቱን በራስ መተማመን ከማዳበር ባለፈ በመሰል ሁኔታዎች ላይ እንደሆነም እርግጥ ነው። በአውስትራሊያ የስፖርት ማዕከል ውስጥ የአዕምሮ ጤና እና ክሊኒካል ሳኮሎጂ ቡድን መሪ የሆኑት ኒኮል ቡራቲን ‹‹ጉዳዩ የግንዛቤ ለውጥ እንደሚያስፈልገውና በግልጽ መነገር ቢጀምር ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ይጠቁማሉ። ይህ ችግር የሚፈጠረው እንደ ኦሊምፒክ ያሉ ታላቅ ውድድሮች ድምቀትና ግርግር ሲቀዛቀዝ ሲሆን፤ ሳምንታት ወይም ወራትን ሊቆይም ይችላል። ውጤታማ መሆን ያልቻሉና ጉዳት የገጠማቸው አትሌቶች ላይ ደግሞ ሁኔታው ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል።

የስፖርት ሳይኮሎጂ ባለሙያዋ ዶክተር ካረን ሆዌልስ በበኩሏ፤ ከስሜት ለውጥ ባለፈ የአዕምሮ መናጋትን ሊያስከትል የሚችልና በሥነልቦና ባለሙያዎች ርዳታ ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ለኒው ዮርክ ታይምስ ጠቁማለች። እስካሁንም በኦሊምፒክ ተሳትፎ ይህን ዓይነት ጉዳይ ያላሳለፈ አትሌት እንዳልገጠማትም እንዲሁ። በአሜሪካ የኦሊምፒክ እና ፓራሊምፒክ ኮሚቴ የሥነልቦና ባለሙያ የሆኑት ጄሲቻ በርትሌ ደግሞ ሁሉም አትሌት ሊደርስበት የሚችለው ጉዳይ አለመሆኑን ይጠቁማሉ። ጉዳዩ ውስብስብ ቢሆንም ስሜቱ ግን በእርግጥም አለ። እአአ በ2023 የተደረገ ጥናት የሆላንድ ብሔራዊ ቡድንን ወክለው በኦሊምፒክ ከተሳተፉ 49 አትሌቶች መካከል 40 ከመቶ የሚሆኑት ይህንን ሁኔታ የተጋፈጡ መሆኑን ያረጋግጣል። በኦሊምፒኩ ውጤታማ የነበሩ አትሌቶችንም የሚያጠቃልል ነው።

ይህ ሁኔታ በአስተሳሰብም ሆነ በቴክኖሎጂ በዘመኑ አትሌቶች ዘንድ በዚህ ልክ የሚከሰት ከሆነ በማደግ ላይ ባሉ የአፍሪካ ሃገራት ደግሞ ምን ዓይነት መልክ ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ እንዲፈጠርና አትሌቶች ላይ ሲያጋጥምም ምን ማድረግ እንደሚገባ ማሳወቅ ተገቢ ነው። የባለሙያዎቹ ምክርም አትሌቶች እና አሠልጣኞቻቸው ከሥነልቦና ባለሙያዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥበቅ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ነው። ባለሙያዎቹም ቢሆኑ ከውድድር በኋላ አትሌቶችን ቀርበው መከታተልና ማማከርም ተገቢ ነው።